በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር

የአራት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

2ኛ ዓመት

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር
የመ.ማ.ቍ. 1252
የስ.ቍ. 51 82 33
አዲስ አበባ

EVERY DAY WITH GOD
4 YEAR BIBLE STUDY COURSE - 2ND YEAR

C BSE, 1995,10M

ይህን ኮርስ በቡድን መከታተል ለሚፈልጉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተሳታፊዎች አስፈላጊውን ምክርና የምስክር ወረቀት ለመስጠት፥ ካስፈለገም ሰሚናር አዘጋጅቶ ለማካሄድ፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ዝግጁ መሆኑን በደስታ ይገልጻል።

በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር

የ1ኛውን ዓመት መጽሐፍ በረከት አይተን፥ የሁለተኛውን ዓመት መጽሐፍ ለእግዚአብሔር ክብርና ለሕዝቡ ጥቅም እንዲሆን እየጸለይን መጽሐፉን በትሕትና እናበረክታለን።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር

አጠቃላይ መግቢያ

በየዓመቱ ተከታታይነት ስላለ የአራቱ ዓመት ፕሮግራም ዓላማ፥ የንባብ ቅደም ተከተል ምክንያት፥ የጥያቄዎች ዓይነት፥ የመግቢያዎችና የግስታወሻዎች ግብ፥ የመጽሐፉ አጠቃቀም፥ ምኅፃረ ቃላት፥ የጥቅስ ምልክት አገባቡ፥ የጥቅስ አወጣጥ ሕግና መጻሕፍቱ የሚጠኑበት ዓመት፥ ከመጽሐፍቱ ስያሜ ጋር የተጠቀሱ ሲሆን፥ ካርታዎችም በ1ኛው ዓመት መጽሐፍ ይገኛሉ።

የሁለተኛ ዓመት ሳምንታዊ ፕሮግራም

እሑድ መዝሙር 52(53)-94(95)

ሳምንት	መጽሐፍ	ሳምንት	መጽሐፍ
1-3	መሳፍንት	27-29	መኃይልየ-መኃልይ ዘሰሎሞን
4-5	ፊልጵስዩስ	29-31	1ኛ ነገሥት (12-22)
6	ሩት	31-34	2ኛ ቆሮንቶስ
7-10	ግርቆስ (1-8)	35-38	2ኛ ነገሥት
10-14	1ኛ ሳሙኤል	38-40	ኤፌሶን
14-18	ግርቆስ (9-16)	40-45	ኢሳይያስ (1-37)
18-21	2ኛ ሳሙኤል	46-47	ቈላስይስ
21-26	1ኛ ቆሮንቶስ	48-52	ኢሳይያስ (38-66)
26-27	1ኛ ነገሥት (1-11)	52	ፊልሞና

የክለሳ ጥያቄዎች ---------- ገጽ 180

ሳምንት 1 እሑድ — መዝሙር 52(53)

መግቢያ፤ ይህ መዝሙር ከመዝ.13(14) ጋር ተመሳሳይነት አለው።

1. ኃጢአት ሰው፥ ሀ) ከእግዚአብሔር ጋር (ቊ.1-3፥5)፥ ለ) ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ያለውን ግንኙነት እንዴት በከለ (4)?
2. በእግዚአብሔር ሕዝብና በሌሎች ሰዎች መካከል ምን፥ ሀ) ተመሳሳይነት (2-3)፥ ለ) ልዩነት አለ (4፥6)?
3. መዝሙረኛው ስለ ሰው ሁኔታ ሲያስብ ምን ተመኘ(6)?
4. ይህ ትምህርት፥ ሀ) ስለ ራስህ ልብ ሁኔታ፥ ለ) ስለምትጸልይላቸው ሰዎች ምን መመሪያ ይሰጣል?

በማስታወሻ፤ ምናልባት የዚማውን ስም ያመለክታል።

መጽሐፈ መሳፍንት

«መጽሐፈ መሳፍንት» ከኢያሱ ሞት በኋላ እስከ ሳሙኤልና ንጉሣዊው መንግሥት እስከ ተመሠረተበት ድረስ ያለውን የእስራኤል ሕዝብ ታሪክ መዝግቦአል። በዚህ ዘመን ከጠላቶቻቸው እንዲድኑና ሥርዓት ባለው መንገድ እንዲተዳደሩ እግዚአብሔር «መሳፍንት» የተባሉትን ጀግኖች አስነሣላቸው። እነዚህ መሳፍንት 12 ሲሆኑ ከሁሉ የታወቁትና በአዲስ ኪዳን የተጠቀሱት ባርቅ፥ ጌዴዎን፥ ዮፍታሔና ሶምሶን ናቸው። ኢያሱ ከሞተ በፊት የእስራኤል ነገዶች አገሩን እንዲይዙ አዘአቸው ነበር (ኢያሱ ም.23-24)፥ ነገር ግን በልዩ ልዩ ምክንያት በከፊል ብቻ ትእዛዙን ፈጸሙት።

ሳምንት 1 ሰኞ — መሳፍንት 1፥1-36፤ 2፥1-5

1. የይሁዳና የስምዖን ነገዶች የደቡብን ምድር ለመውረስ እንዴት ጀመሩ (1፥1-20)?
2. ይሁዳና ብንያም ምንን ለመውረስ አልቻሉም (1፥19-21)? ለምን?
3. ሌሎች ነገዶች ከከነዓናውያን ጋር እንዴት መኖር ጀመሩ (1፥22-36)?
4. የእስራኤል ሕዝብ አለመታዘዝ ውጤት ምን ነበር (2፥1-5)?
5. በሕይወታችን ልዩ ልዩ ችግር የሚፈጠርብን ወላጆቻችን ወይም እኛ ለእግዚአብሔር ባለመታዘዛችን ነው (2፥23)። አንተ ይህን የመሰለ አጋጥሞህ ያውቃልን?

1፥1 ግን በፊት ይመልከቱ፤ ኢያሱ ከነዓናውያንን በመርከት እዘንር ነበር፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ነገድ የራሱን ርስት መውረስ ነበረበት፤ 2፥6፤ ኢያሱ 13፥1፤ 14፥1።

1፥12-15፥20 ካሌብ፤ ኢያሱ 15፥15-19።

1፥19 የብረት ሰረገሎች፤ እስራኤል እነዚህን መሣሪያዎች እጅግ በመፍራታቸው የእምነታቸውን ጉድለት ገለጡ፤ ዘዳ.20፥1፤ ኢያሱ 17፥16-18፤ መሳ.4፥13-15።

1፥21 ኢየሩሳሌም፤ በይሁዳና በብንያም መካከል በነበረው ድንበር የሚገኝ ነው። በጽዮን ተራራ ላይ የተሠራ የከተማው ዋና ምሽግም እስከ ዳዊት ዘመን ድረስ በኢያቡሳውያን እጅ ቀረ።

1፥27 ቤትሳን ... መጊዶ፤ እነዚህ ከተሞች በሰሜን ነገዶች (ዛብሉን፥ ይሳኮር፥ አሴር፥ ንፍታሌም) እና በመሐል ነገዶች (ኤፍሬም፥ ምናሴ፥ ዳን) መካከል በከነዓናውያን እጅ በመቅረታቸው የእስራኤልን አንድነት አዳከሙ።

1፥35 ኤሎን፤ በምዕራባዊ ሰሜን አትጣጪ ከኢየሩሳሌም 17 ኪ.ሜ. የሚርቅ፥ በይሁዳ (ከብንያምና ከስምዖን ጋር)ና በኤፍሬም ነገዶች መካከል የነበረ የከነዓናውያን ከተማ። እንግዲህ የእስራኤል ነገዶች በአራት ተከፈሉ፤ ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ፥ በደቡብ፥ በመሐልና በሰሜን ያለውን (ካርታ ተመ.)።

ሳምንት 1 ማክሰኞ — መሳፍንት 2፥6-23፤ 3፥1-6

1. «አመነዘሩ» የሚለውን ቃል አብራራ (2፥11-17)።
2. በ2፥11-19 ውስጥ ከግፈግፈግ፥ ከፍርድ፥ ከመለመን፥ ከመዳንና እንደገና ከግፈግፈግ ... ወዘተ የሚታየውን ዑደታዊ ሁኔታ ግለጥ።
3. የእግዚአብሔር ሕዝብ መታዘዝ ከመሪዎቻቸው መታዘዝ ጋር ምን ያህል የተሳሰረ ነበር (2፥6-19)? ዛሬስ?
4. የሚመጣው ትውልድ እግዚአብሔርን እንዲያውቅ በበኩልህ ምን ማድረግ ትችላለህ (2፥10፤3፥6)?
5. ሌሎች ሕዝቦች በእስራኤል መካከል እንዲኖሩ ምን ምስት ምክንያቶች ነበሩ (2፥20-3፥6)?
6.* በ1፥19፤ በ2፥1-55 በዘጸ.23፥29 ምን ሌላ ምክንያት ታገኛለህ? እግዚአብሔር በተስፋ ቃሉ የሰጠህን ርስት ሁሉ እንዳትወርስ ምን ምክንያት አለ?

2፥11 በአሊም፤ በየቦታው የበአል ጣዖታት ነበሩ፤ በአል የዝናብና የልምላሜ አምላክ ነበረ፤ ቃሉ ደግሞ ባሎችን ሊያመለክት ስለሚችል «አመነዘሩ» ለሚለው ግስ የበለጠ ፍች ይሰጣል።

2፥13 አስታሮት፤ በከነዓናውያን የተከበሩ የልምላሜ፥ የፍትርና የጦርነት ሴት አምላክ ምስሎች ነበሩ፤ በስማቸውም ብዙ ነውር ይፈጸም ነበር።

2፥19 የከፋ ያደርጉ ነበር፤ በዑደታዊ ሁኔታቸው ከሀዲታቸው በየጊዜው ባሰ።

ሳምንት 1 ረቡዕ — መሳፍንት 3፥7-31

1. እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ምን አመጣባቸው (ቊ.8-12)? ለምን (7፥12)?
2. እግዚአብሔር ለእስራኤል ምን አደረገ (9፥15)?
3. ጎቶንያል (ዖትንኤል)፤ ናያድ (ኤሁድ)ና ሰሜጋር (ሻምጋር) እስራኤልን ለማዳን በምን አኳኋን ቻሉ?
4. እግዚአብሔር አንድን ሰው ለልዩ ሥራ ሲያስነሣ አይተህ ታውቃለህን? ከዚህ ሰው ጋር እንዴት ትተባበራለህ?

5.* ከ12ቱ መሳፍንት በዛሬው ምንባብ በተጠቀሱት በሦስቱ መሳፍንት ጀምረህ፥ ሀ) ስም፥ ለ) ነገድ፥ ሐ) ጠላት፥ መ) እስራኤል ለዚህ ጠላት የተገዛበት ዘመን፥ ሠ) ያሸነፈበት ዘዴ፥ ረ) የድሉ ምክንያት ፥ ሰ) ጉድለት ወይም ስሕተት፥ ሸ) የአገልግሎቱ ዘመን፥ ቀ) ከሥራው የተነሣ የነበረው የሰላም ዘመን፥ በ) ስለ አገልግሎቱ ሌላም ተጨማሪ ነገር ካለ በሠንጠረዥ ግለጥ።

ሮሜ.9 ጎቶንያል፤ 1፥11-15። ጠላት ከሰሜን ሲመጣበት ጎቶንያል የይሁዳ ሰው ቢሆንም ነገዶችን ለማስተባበር ቻለ።

ሮሜ.12 ሞዓብ፤ ዘፍ.19፥30-38፤ ዘኍ.21፥20-31፤ 25፥1-5፤ ዘዳ.23፥3-4።

ሮሜ.13 ዘገባባሮ ያለባትን ከተማ፤ ኢያሱ።

ሳምንት 1 ሐሙስ — መሳፍንት 4 እና 5

1.* ታሪኩን እያነበብህ ትናንትና የጀመርኸውን ሰንጠረዥ ሙላ።

2. በእስራኤል ድል፥ ሀ) የእዝአብሔር፥ ለ) የዲቦራ፥ ሐ) የባርቅ፥ መ) የኢያዔል ፈንታ ምን ነበር (4፥4-22)?

3. ከሦስቱ ሰዎች በእምነቱ የትኛው ታወቀ (ዕብ.11፥32-33)? ለምን?

4. በእምነት እንድትበረታ ከዚህ ታሪክ ምን ትማራለህ?

5.* የቅኔው መንፈስ ስለ፥ ሀ) ንፍታሌም ከተማ ሜርዝ (5፥23)፥ ለ) ኢያዔል (5፥24-27)፥ ሐ) ሲሣራ እናትና ጠላቶች (5፥28-31) ለክርስቲያን ተገቢ ነውን?

4፥14 እግዚአብሔር በፊትህ ወጥቶአል፤ የኢይዝራኤል ሜዳ ለብረት ሰረገሎች ጦርነት ምቹ ሲሆን፥ ዝናብ በኃይል በሚዘንብበት ወቅት የቂሶን ወንዝ ሞልቶ ሜዳውን በመሸፈን የሰረገሎችን መንኰራኵሮች በጭቃ ይይዝ ነበር።

5፥24 ቄናዊው፤ 1፥16።

ሳምንት 1 ዓርብ — መሳፍንት 6

መግቢያ፤ ምድያማውያን የሚባሉ ዘላኖች ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ይኖሩ ነበር፤ በየዓመቱ ወንዙን ተሻግረው ከእስራኤል ነገዶች እርሻ ፍሬ ይዘርፉ ነበር።

1. የእስራኤል ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ሲጮኹ በመጀመሪያ ምን ተደረገላቸው (ቊ.1-10)? ለምን?

2. መልአኩ ለጌዴዎን ጥያቄዎች ምን መልስ ሰጠ (11-18)?

3. ጌዴዎን ለእግዚአብሔር መሠዊያ ከመሥራቱ በፊት ምን ምን ለማድረግ ታዘዘ (22-27)?

4. ጕረቤቶቹ ጌዴዎንን ሲቃወሙ ሌሎች ለምን ተከተሉት (28-35)?

5. ጌዴዎን በተሰጡት ምስት ምልክቶች ምን መማር ቻለ (19-21፤36-40)?

6. ከዚህ ምዕራፍ ስለ እግዚአብሔር አመራር ምን ታስተውላለህ?

ሮሜ.11 ዮፍራ፤ ከዮርዳኖስ በስተ ምዕራብ በምናሴ የነበረ ስፍራ።

ሉ.25 የገምሶክያ ዐይድ፤ የ2፥13ን ግስታመሻ ተመ.።

ሉ.33 በኢይዝራኤል ሽለቆ፤ የ1፥27ን ግስታመሻ ተመ.።

ሳምንት 1 ትዳሜ — መሳፍንት 7

1፤ ሰዎች ለጦርነት በምን መሠረት ተመረጡ (ሉ.1-8)?

2. ጌዴዎን የጦርነት ፅድ እያለው ሲጠራጠርና ሲፈራ ሳለ (8-10)፥ እግዚአብሔር ወደ ሙሉ መተማመን እንዴት አደረሰው (11-15)?

3. «ለእግዚአብሔርና ለጌዴዎን» የሚለው ጩኽት ስለ መንፈሳዊ ጦርነት ምን ያስተምራል?

4. በውጊያው የሆነውን ዘርዝር (19-25)።

5. ዛሬ እግዚአብሔር ሰዎችን ለሥራው እንዴት ለይቶ ያዘጋጃቸዋል?

ሉ.6 ውኃ ሊጠጡ በጉልበታቸው ተንበረከኩ፤ ምድያማውያን ፀድንቱት አደጋ ቢጥሉባቸው ኖር ለጦርነቱ ዝግጁ አልነበሩምና ለከባድ ጦርነት ብቁ አልነበሩም።

ሉ.22 መራሮቱ ... ሸሹ፤ የጉርዳኖስን መንገ ለመሻገር።

ሉ.23 9700 ሰዎቹ በትርብ የቀሩ ይመስላል (3፥8)።

ሳምንት 2 እሑድ — መዝሙር 53(54)

1፤ ዳዊት የነበረበትን ሁኔታ ግለጥ (ሉ.31 1ሳሙ.23፥19-20)።

2. እግዚአብሔር ምን እንዲያደርግለት ለመነ (1-2)?

3. የዳዊት እምነት በምን ይታያል (4-7)?

4. አንተ «በእውነትህም አጥፋቸው» ብሎ መጸለይ ይገባሃልን (5)? ለምን?

5. በትርብ ጊዜ ስትጨነቅ፥ ሀ) በምን አኳኋን ወደ እግዚአብሔር ጸለይህ? ለ) እግዚአብሔር ምን አደረገልህ?

ሉ.5 አጥፋቸው፤ መዝ.5፥10 እና ግስታመሻውን ተመ.።

ሳምንት 2 ሰኞ — መሳፍንት 8

1.* ታሪኩን ተከታትለህ ስለ ጌዴዎን ሰንጠረዥን ሙላ።

2. ጌዴዎን፥ ሀ) የኤፍሬምን ሰዎች በሰላም በግናኙ (ሉ.1-3)፥ ለ) በ300 ሰዎች ምድያማውያንን በግሳደዱ (4፥10-12)፥ ሐ) የሱኮትንና የፔንኤልን ሰዎች በመቅጣቱ (5-9፥13-17)፥ መ) ዛብሄልንና ስልግናን በመግደሉ (18-21)፥ ሠ) ጎሾ መሆን ባለመፈለጉ (22-23) ስለ ጌዴዎን ታላቅነት፥ እምነትና ጠባይ ምን ታስተውላለህ?

3. ጌዴዎን ይህን ሁሉ ካደረገ በኋላ ምን ስሕተት ሠራ (24-32)? እንደ በፊቱ የእግዚአብሔርን መሪነት ለምን አልጠየቀም (24-32)? የስሕተቱ ውጤት ምን ነበር (27-35)?

4. አንተ በእግዚአብሔር እየተመራህ ከኖርክ በኋላ በራስህ በመተማመን ሒደህ ታውቃለህን? ለምን? ምን ሆነ?

ዮ.1-3 ይህም የሆነው ጌዴዎን ከዘመቻ ሲመለስ ይሆናል፤ በዚህ ዘመን ኤፍሬም በወንዞቹ መሻገሪያ መጠነኛ ብልጫ ነበረው።

ዮ.10 ቁርቁር፤ ከጨው ባሕር በስተ ምሥራቅ የነበረ ስፍራ።

ዮ.26 1700 ሰቅል ወርቅ (20 ኪሎ ያህል)፤ የድሉን ታላቅነት ያሳያል።

ዮ.27 ኤፉድ፤ በዚህ አማካኝ ታሉ፥ ጌዴዎን የእግዚአብሔርን ረቃድ ለማወቅ የጠየቀበት ምስል ይመስላል።

ዮ.31 አቤሜሌክ፤ የቁባቱ ልጅ በመሆኑ በጌዴዎን ዐተሰብ ላይሆን በእናቱ ዐተ ሰብ ተቈጠረ፤ ቁባቱም ከነዓናዊት ሳትሆን አልቀረችም (9፥4ና ማስታወሻ፤ ዘዳ.7፥1-3)።

ሳምንት 2 ማክሰኞ

መሳፍንት 9

መግቢያ፤ በዚህ ምዕራፍ ከአሥራ ሁለቱ መሳፍንት የሚታረን ያላግባብ የአሰራሌልን ሕዝብ ለመምራት የተነሣው ከከነዓናዊት ቁባቱ የተወለደውን የጌዴዎን ልጅ የነበረውን የአቢሜሌክን ታሪክ መዝግቦአል (8፥23)።

1. አቢሜሌክ የሴኪም ንጉሥ ለመሆን እንዴት ቻለ (ቍ.1-6)?
2. በኢዮአታም ምሳሌ፥ የሴኪም ሰዎችና አቢሜሌክ በምን ተመሰሉ? እንዴትስ ረገማቸው (7-21)?
3. እግዚአብሔር በአቢሜሌክና በሴኪም ሰዎች ላይ ምን አደረገ? ለምን (22-24)?
4. የኢዮአታም እርግማን እንዴት ተፈጸመ (25-27)?
5. ከሱ ሰዎች ሊለያዩና ሊፋጁ አይተህ ታውቃለህን?
6. ከዚህ ታሪክ ለጸሎትህ ምን መመሪያ ታገኛለህ?

ዮ.4 በኣልብሪት፤ የበኣል ኪዳን ማለት ነው፤ የሴኪም ሰዎች በኣልን አምላኪና ከነዓናውያን ነበሩ 28፤ዘፍ.33፥19።

ዮ.15 እሳት ከአቺህ ይውጣ፤ በበጋ ከደረቅ እሾህ የሚነሣ እሳት ሰደድ በመሆን ብዙ ጊዜ የዝግባ ዛፎችን ያቃጥላል።

ሳምንት 2 ረቡዕ

መሳፍንት 10

1. የቶላና የኢያዕር አገሮች የት ነበሩ? ምን ሠሩ (ቍ.1-5)?
2. የእስራኤልን ኃጢአት በርግር (6፥13)።
3. በእውነት ንስሓ እንዲገቡ እግዚአብሔር ምን አደረገ?
4. ይህ ምዕራፍ ስለ እግዚአብሔር፥ ሀ) ቍጣ፥ ለ) ርኅራኄ ምን ያሳያል?
5. ኃጢአት ከመራህ በኋላ ንስሓ እስክትገባ ድረስ ምን ያህል ጊዜ ትዘገያለህ? ለምን?
6. * ለንጠረጥህን ሙላ።

ዮ.3 ኢያዕር፤ ከዮርዳኖስ በስተ ምሥራቅ ከምናሴ ወገን የነበረ መስፍን።

ሳምንት 2 ሐሙስ

መሳፍንት 11

1. የፍታሔን ጀግና እንዲሆን የገፋፋው ምን ነበር (ቍ.1-11)?


2.* ዮፍታሔ አሞንን ሲታገል በትክክለኛነት ለመሔዱ ምን ማስረጃ ነበረው (12-28፤ በተለይ 21፡23)?

3. ዮፍታሔ የእምነት ሰው እንደነበረ ምን ማስረጃ አለ (11፡24፡27፡29-31፡35፤ 12፥3፤ ዕብ. 11፥32-33)?

4.* የዮፍታሔ ስሕተት ምን ነበር (31፤ ዘዳ. 12፥31፤ መክ. 5፥2-6)?

5. የሚከተሉት ዓበይት ነጥቦች ከሕይወትህ ጋር ምን ያህል የተሳሰሩ አለዚያም የተለያዩ ናቸው? ሀ) የእድገት ሁኔታ፥ ለ) ሰዎች በእንተ ላይ ያላቸው መተማመን፥ ሐ) የእግዚአብሔር ቃል እውቀትህ፥ መ) የእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ እውቀትህ፥ ሠ) በሕይወትህ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ።

6. የዮፍታሔን ሴት ልጅ እምነትና አድራጎት ከራስህ ጋር አስታያይ (34-40)።



ቍ.31 ለሚታወልም መሥዋዕት አትርበየለሁ፤ ስእለቱን ለመፈጸም አንድ ልጁን ለመሠዋት ግዴታ እንደነበረበት አወቀ (ዘኍ. 30፥2፤ ዘዳ. 23፥21-23)፥ ሆኖም በአሕዛብ የሚሠዉ የሰው መሥዋዕቶች በእግዚአብሔር ፊት አጸያፊ መሆናቸውን አላወቀም፥ በጦብ ምድር የሕግ መምህር የነበረ አይመስልምና (3)፤ ሆኖም የአገሩን የፖለቲካ ታሪክ በደንብ አወቀ (12-26)።

<u>ሳምንት 2 ዓርብ</u> <u>መሳፍንት 12</u>

1. የኤፍሬም ሰዎችን ስሕተት ዘርዝር (ቍ. 1-4፤ 8፥1-3)።

2. ለኤፍሬም ሰዎች መልስ ሲሰጡ በጌዴዎንና በዮፍታሔ መካከል ምን ልዩነት ነበረ (8፥3ን ከ12፥3 ጋር አነጻጽር፤ ምሳ. 15፥1)?

3. የዚህ ጠብ ውጤት ምን ነበረ (5-6)?

4.* ስለ መሳፍንት ሰንጠረዥህን ሙላ (7-15)።

5. የአንተ መንፈሳዊ ሁኔታ በአንድ መሪ ላይ ምን ያህል የተመረኮዘ ነው?

ሳምንት 2 ቅዳሜ

መክፍት 13

1. መክፍን ለመሆን የሶምሶን ጥሪ ከሌሎች መክፍንት በምን ይለያል (ቍ. 1-7)?
2. ከዚህ ቤተሰብ ስለ ጋብቻ ምን ትማራለህ (6-14)?
3. እንርሱ ስለ እግዚአብሔር አመራር ምን ተረዱ (15-23)?
4. እግዚአብሔር በሕይወትህ አንድ ልዩ ነገር ሊያደርግ ስሜትህንና አድራትትህን ከማኑና ከሚስቱ ጋር አስተያይ።

ቍ. 1 ናዝአዊአችሁ፤ በዋጌው ከክፍር በተርጨለ) እና ከሌላ እንር እየረሌሱ በክሳን እንር እየሰሙ ሔዱ (3፥31፤ 10፥7፤ ዘፍ. 21፥32-34፤ ኦሾጽ 9፥7)፤ በእግር ጊዜ ከሚሔሩ ዳር አጠገብ ሳለው ሚዳ እያስት ከተማዎችን (ጋዛ፥ አስቀሎና፥ ጌት፥ አቃሮን) በመሥሪታቸው የአየራውያንን እንር አሳጨ፤ አሞራውያንም በተራቸው የሳንን ነገድ ርስት በግጫሳቸው የሳን ነገድ እንድ ከፍል ደግሞ ወደ ሰሜን ረሌለ፤ 1፥34-36፤ ዮ. 18።

ቍ. 2 ጸርጋ፤ ከኢየሩሳሌም በስተ ምዕራብ 22 ኪ.ሚ. የሚርት ትንሽ ከተማ።

ቍ. 5 ናዝራዊ፤ ዘኁ. ም. 6 ተመ.።

ሳምንት 3 እሑድ

መዝሙር 54(55)

መዝሙር፤ ኢየሩሳሌም በጠላቶችዋ ስትከበብ ዳዊት እግዚአብሔር እንዲረዳው ያጸልያል፤

1. ዳዊትን ያስጨነቀውን ሐሳብ ግለጥ (ቍ. 2-5)።
2. ምን ማድረግ ረሰገ (6)? ለምን (6-8)?
3. ስለ ጠላቶቹ ሲጸልይ ከሁሉ በላይ የሚያሳዝነው ሁኔታ ምንድን ነው (9-14፥20-21)?
4. ወደ እግዚአብሔር ሲመኸ ተስፋ የሚሰጠት ምን ሐሳቦች ነበሩት (16-19፥22-23)?
5. የቅርብ ዘመድህ ወይም ጓደኛህ ከድተህ ያውቃል? ምን አደረግህ?

ቍ. 12-14 መዝ. 40(41)፥9 ተመ.።

ሳምንት 3 ሰኞ

መክፍንት 14

1. ሀ) ሶምሶንና ወላጆቹ ስለ ጋብቻ ምን ሐሳብ ነበራቸው (ቍ. 1-4፤ ዘዳ. 7፥1-3)? ለ) እግዚአብሔርስ በሶምሶን ፍላጎት እንዴት ተጠቀመ?
2. ሶምሶን የናዝራዊትነቱን ስእለት እንዴት ነቀረ (5-9፤ ዘኁ. 6፥6-9)?
3. የሚስቱ ጠባይ እንዴት ነበር (10-17)?
4. ሶምሶን ለሚስቱ ገበነዛ እጅ ሲሰጥ እግዚአብሔር እንዴት ተጠቀመበት (18-20)?
5. ለምቾ ሲል ከመንዙህ ምን ታደርጋለህ?

ቍ. 1 ተምና፤ ከዳርን 6 ኪ.ሚ. የሚርት ስፍራ።

ቍ.4 እግዚአብሔርም ... ምክንያት ይፈልግ ነበር፤ ፍልስጤማውያን በእስራኤላውያን ላይ እንደ ሌሎቹ የእስራኤል ጠላቶች አልሆኑባቸውም፤ ይሁን እንጂ ኢኮኖሚያቸውን፥ ባህላቸውንና ሃይማኖታቸውን አስርገው በማስገባት ዓይነተኛ የእስራኤል መታወቂያ የሆነውን የእግዚአብሔር ሕዝቡት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ አደጋመው ነበር። እግዚአብሔር በእስራኤልና በፍልስጤማውያን መካከል ጠላትነትን ለመፍጠር በሶምሶን ተጠቀመ፤ ሲጠቀምበትም አንሶ በተገኘበት እንጂ የእግዚአብሔር ሰው ሆኖ መቆም በነበረበት ጠባይ አልነበረም፤ ሐ.መ.2፥23።

ቍ.19 አስትስና፤ ከተምና 35 ኪ.ሜ. የሚርቅ ከተማ።

ሳምንት 3 ማክሰኞ — መሳፍንት 15

1. የእግዚአብሔር ዓላማ (14፥4) ፈጻሚ የሆኑትን የሶምሶን ድርጊቶች ዘርዝር (ቍ.3-17)?
2. ሶምሶን ስለ በቀል ያልተረዳው ነገር ምን ነበር (7-10)?
3. በዚህ ጊዜ ሶምሶን በምን ዓይነት መንፈስ ለመነ (18-19)?
4. ስትሠቃይ በምን መንፈስ ትጸልያለህ?

ቍ.1 የፍየል ጠቦት፤ ሚስት ከመጀኗ ጋር በቆየች ጊዜ ባል የሚያተርፀው የተለመደ ስጦታ የነበረ ይመስላል።

ቍ.4-5 በሰው ኃጢአት ምክንያት ፍጥረት ይሠቃያል፤ ሮም 8፥21-22።

ቍ.6 ልቲትንና አባትዋን በእሳት አቃጠሉ፤ 14፥15።

ቍ.8 ዋን ጭናቸውን ብሎ (ብርቱ አደጋ ጣለባቸው)፤ የዘመኑ አነጋገር ይመስላል።

ቍ.14 የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ወረደበት፤ 3፥10፤ 6፥34፤ 11፥29፤ 13፥25፤ 14፥6፥19። መሳፍንቱ ቅዱሳን ሰዎች ባይሆኑም በእግዚአብሔር ኃይል ድል ነሡ፤ የእግዚአብሔር ስጦታዎች የአምላክን ቸርነት እንጂ የሰውን ልፅልና አያረጋግጡም። የ14፥4ን ማስታወሻ፤ የበለዓምን ታሪክ በዘኁ.ም.22-24፤ ግቴ.7፥21-23፤ 1ቆሮ.13፥1-3 ተመ.።

ሳምንት 3 ረቡዕ — መሳፍንት 16

1. ሶምሶን የጋዛን በር ወደ ኬብሮን ለምን አመጣ (15፥11-13)?
2. የፍልስጤማውያን መኳንንት ሶምሶንን ከወዲሁ ለመግደል ለምን አልፈለጉም (2፥4-5፥21-25)?
3. ሶምሶን በምን ምክንያት ተያዘ (4፥15-20)?
4. መንፈሳዊ ነፃነት እስኪጠፋብህ ድረስ ምን ሊያጸክምህ ይችላል?
5. ሶምሶን በመጨረሻ ጸሎቱ እምነቱን እንዴት ገለጠ (28-30፤ ዕብ.11፥32-33)?
6. * ሰንጠረዥህን ሙላ።

ቍ.1 ጋዛ፤ ከኬብሮን 60 ኪ.ሜ. የሚርቅ ከተማ የ13፥1ን ማስታወሻ ተመ.።

ቍ.16 ነፍሱቸው፤ 14፥16-17።

ቍ.21 እህል ይፈጭ ነበር፤ የሴት ሥራ።

ዮ.28 እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፥ እሻህ፤ አውን በእግዚአብሔር ፊት መገረሱ እንደተለመጠ ይታያል 14፥3፤ 15፥18።

ሳምንት 3 ሐሙስ — መሳፍንት 17 እና 18

መግቢያ፤ ጸሐፊው እግዚአብሔር ሕዝቡን በምን መሠረት እንደሚገዛ ካስረዳና (ም.1-2)፥ የ12ቱን መሳፍንት ታሪክ ከመዘገበ በኋላ (ም.3-16)፥ ስለ ዳንና ስለ ብንያም ነገዶች ሁለት ታሪኮችን ያቀርባል። እነዚህ ታሪኮች በምን ጊዜ እንደሆኑ ባናውቅም፥ በመሳፍንቱ ዘመን የነበረውን የእስራኤልን ሁኔታ ይገልጣሉ።

1. የሚካ ሐሳብ ስለ እግዚአብሔር እንዴት ነበር (17፥5፡13)?
2. የዳን ሰዎች ስለ ሃይማኖት የነበራቸው ሐሳብ እንዴት ነበር (18፥5-6፡10፡14፡27፡31)?
3. እንደ ሚካና እንደ ዳን ሰዎች ልዩ ልዩ ነገር ወይም ሰው በረከትን የሚያስገኝልህ ይመስልሃልን?

17፥5 ኤፉድ፤ 8፥27ና ግስታወሻውን ተመ.።

ተራፊም፤ በሰው መልክ የተሠሩ ምስሎች።

18፥1 ለዳን ነገድ፤ 1፥34-35፤ የ13፥1ን ግስታወሻ ተመ.።

18፥7፡29 ሌሳ ... ዳን፤ ከኢየሩሳሌም 160 ኪ.ሜ. የሚርቅ ከተማ።

ሳምንት 3 ዓርብ — መሳፍንት 19፥1-30፤20፥1-13

1. ስለ ሌዋዊው ጠባይ ከአድራጎቱ ምን ታስተውላለህ (19፥1-3፡12፡25፡29)?
2. የዚያ ዘመን ሐሳብ ስለ፥ ሀ) እንግዳ ተቀባይነት፥ ለ) ሴቶች እንዴት ነበር (19፥22-26፤20፥4-7)?
3. የእስራኤል ሕዝብ ንጉሥ ባይኖራቸውም ምን ያህል አንድነት ነበራቸው (19፥1፤20፥8-13)?
4. በአካባቢህ፥ ሀ) የሥነ ምግባር፥ ለ) የአስተዳደር፥ ሐ) የአንድነት ሁኔታ ምን ይመስላል?

19፥2 አመነዘረችበት (ልጅቱ ከአርሱ ጋር ተጣልታ)።

19፥22-24 ሰዎች አንድን ነገር በሚገባ ቢያስተውሉም፥ ስለ ሌላ ጉዳይ ፍጹም ዕውራን ሊሆኑ ይችላሉ፤ ዘፍ.19፥4-9።

ሳምንት 3 ቅዳሜ — መሳፍንት 20፥14-48፤ 21፥1-25

1. በመጀመሪያውና በሁለተኛው ቀን ምን ሆነ (20፥14-25)? ለምን?
2. እስራኤል በብንያም ላይ የነበረው ስሜት እንዴት ተለወጠ (20፥18፡23፡26-28)?
3. ካሸነፉአቸው በኋላ እስራኤል ስለ ብንያም ምን ተሰማቸው (21፥1-6)?
4. ከብንያም ዘር እንዳይጠፉ እስራኤል ምን አደረገላቸው (21፥7-23)?

5. ታል ከመግባትህ ወይም እርምጃ ከመውሰድህ በፊት፥ የገጡን የመጨረሻ ሙሉት በእግዚአብሔር ፊት ትመረምረዋለህን?

6. ከሁለም ክርስቲያኖች ጋር እንድትትህን እንዴት ትገልጣለህ?

<u>2ዎ፥16 ገራኝ ሰዎች</u>፤ 3፥15።

<u>20፥27 ታሪት</u>፤ ከሳን ከተያዘ በኋላ ታቦቱ በአጉ መሐል በልዩ ልዩ ስፍራ ፦ በአሕድ፥ በሌሎ፥ በቤተልና በመጨረሻም ተመለሰ በሚሉ ይተመተ ነበር፤ 18፤ 18፥31፤ 21፥2፤ ኢያሱ 24፤ 14መ. 1፥9፤ 3፥15።

<u>21፥25 በዚያም ዘመን በእስራኤል ዘንድ ንጉሥ አልነበረም</u> (17፥6፤ 18፥1፤ 19፥1)፤ መጽሐፉ የተጻፈው የነገሥታት ሥርዓት በእስራኤል ላይ ከጸና በኋላ ይመስላል።

<u>ሳምንት 4 እሑድ</u> <u>መዝሙር 55(56)</u>

<u>መዝሙር</u>፤ በ1ኛ ሳሙ. 21፥10 ላይ ዳዊት ወደ ጌት ከተማ በመሄዱ በራሱ ሕዝብ ምንም ተስፋ እንዳልነበረው እናያለን። ጌት በዳዊት የተገደለው የፍልስጥኤማውያን ጀግና የነበያድ ከተማ ነበር (1ሳሙ. 17፥4፥45-50)። ይህ የሚገልጥት ጊዜ ካለፈ በኋላ ዳዊት ለእግዚአብሔር ያቀረበው ምስጋና በመዝ. 33(34) ተጽፎ ይገኛል።

1. ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር ሊነጋገር ስለሚያስችገረው ሁኔታ ምን ገለጠ (ቊ. 1፥2፥5፥6)?

2. ተመሳሳይ የሆነ ፈተና ደርሶብህ ያውቃልን? ከሆነ በፍርሃትና በእምነት መካከል እንዴት እንደመላመልህ ግለጥ።

3. ሀ) የእግዚአብሔር ፍቅር ለዳዊት በምን ይታያል (8)? ለ)ዳዊት ይህን ተረድቶ እንዴት ተጽናና (9)?

4. የዳዊት እምነት በእግዚአብሔር እንዴት እንዳደገ ግለጥ (3-4፤ 10-11፤ 12-13)።

5. እግዚአብሔር ላንተ በችግር ጊዜ ምን የሚያጽናና ሐሳብ ሰጠህ?

ሬልጵስዩስ

ሬልጵስዩስ በመቄዶንያ ከታወቁት ከተሞች አንዱ ነበር። በዚያም ልድያ የወንጌልን ታል እንድታዳምጥ ጌታ ልብዋን ከፈተላት፤ ጳውሎስም በዚያ የምኵርተኝነትን መንፈስ ከአንዲት ገረድ ካወጣ በኋላ ተደብድቦ በወኅኒ ተጣለ፤ የወኅኒ ጠባቂ የነበረውም ከቤተ ሰቡ ሁሉ ጋር አምኖ ተጠመቀ (ሐ.ሥ. 16፥9-40)፤ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የሬልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ጳውሎስን በመንፈል ሥራው ረዳቸው። ጳውሎስም ይህን መልእክት ከወኅኒ ቤት ጻፈ። ብዙዎች ሊታውንት እንደሚያስቡት ታስሮ የነበረው በርም ከሆነ፥ የሬልጵስዩስን ቤተ ክርስቲያን ካቋቋመ ከ15 ዓመት በኋላ ይህን መልእክት ጽፎታል ማለት ነው።

ሳምንት 4 ሰኞ — ፊልጵስዩስ 1፥1-11

1. በጳውሎስና በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን መካከል የነበረውን ግንኙነት አብራራ (ቊ.1-2፥7-8)።
2. ሐዋርያው በደስታ ለምን ያመሰግን ነበር (3-7)?
3. የወንጌል ሥራ መሪዎች ስለ ትብብርህ፥ ሀ) በወንጌል፥ ለ) በስደት ችግር ምክንያት ምን ያህል ሊያመሰግኑህ ይችላሉ?
4. ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ምእመናን ምን አራት ነገሮችን ለመነ?
5. እነዚህን ነገሮች አንተ ለሌሎች ከምትለምነው ጋር አስተያይ።
6.* በፊልጵስዩስ ምእመናን ላይ የነበረው የጳውሎስ መተማመን በምን ላይ የተመሠረተ ነበር?

ቊ.1 ጢሞቴዎስ፤ ወንጌል መጀመሪያ በፊልጵስዩስ ሲሰበክ የጳውሎስ አገልጋይ ነበር፤ 2፥19-23፤ ሐ.ሥ.16፥1-3።

ከኤጲስ ቆጶሳት መሪዎች ጋር፤ ጳውሎስ መልእክቱን የጻፈው የክርስቶስ አካል ለሆኑ «ለትጉሳን» ሁሉ ሲሆን፥ የኤጲስ ቆጶሳትን እና የዲያቆናትን ሥልጣን አልነቀፈም፤ ሐ.ሥ.20፥28።

ቊ.6 መልካምን ሥራ የጀመረው ... እስኪፈጽመው፤ አማኞች በክርስቶስ ቅዱሳን (ቊ.1) ግለትም የተለዩ ቢሆኑም፥ ፍጹማን አይደሉም፤ ፍጹምነት በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ብቻ ሙሉ ይሆናል።

ሳምንት 4 ማክሰኞ — ፊልጵስዩስ 1፥12-18

1. የጳውሎስ መታሰር ለወንጌል መስፋፋት እንዴት ምክንያት ሆነ (ቊ.12-14)?
2. አንተ ወይም ሌሎች ብትታሰሩ ምን ታስባለህ? ለምን?
3. የወንጌል እውቀት በምን ሁለት መንገድ ሊታወቅ ይቻላል (15-17)?
4. ጳውሎስ ለምን ተደሰተ (18)? አንተስ?

ቊ.12 የደረሰብኝ፤ በኢየሩሳሌም መያዙና በቄሣርያና በሮም በልዩ ልዩ ባለ ሥልጣናት ፊት ለፍርድ መቅረቡ፤ ሐ.ሥ.ም.21-28።

ሳምንት 4 ረቡዕ — ፊልጵስዩስ 1፥19-30

መግቢያ፤ ጳውሎስ በወኅኒ ቤት በነበረበት ጊዜ ወጥቶ አገልግሎቱን ሊቀጥል ቢፈልግ፥ የሞት ፍርድ ሊፈረድበት እንደሚችል ያውቅ ነበር፤ ሆኖም ስለሚደርስበት ሥቃይ ብዙ ሳይጨነቅ በመመስከር ጊዜውን ያሳልፍ ነበር (1፥12-13)።

1. ጳውሎስ፥ ሀ) በሕይወት መኖርን፥ ለ) መሞትን እንዴት ተመለከተ (ቊ.19-26)?
2. በሕይወቱ የጳውሎስ ትልቅ ምኞቱ ምን ነበር (20)?
3. ሞትን እንደ «ጥቅም» ለምን ቈጠረ?

4. ስለ፥ ሀ) ሕይወት፥ ለ) ሞት ያለህን አስተያየት ከሐዋርያው ጋር አስተያይ።

5. ክርስቲያን ተታውሞንና ስደትን በምን አኳኋን ሊታገሥ ይገባዋል (27-30)? ለምን?

ቍ.19 ለመዳኔ፤ ከውጫ ቤት ነገ መውጣቱን ያመለከተ ይመስላል።

ቍ.22 የሥራ ፍሬ፤ እግዚአብሔር በእርሱ ይሠራ እንደነበር ሙሉ መተማመን ነበረው።

ቍ.29 መከራ ደግሞ ልትቀበሉ፤ እንደ እምነት መከራን መቀበል የእግዚአብሔር ስጦታ ሆኖ የመዳን ምልክት ነው።

ሳምንት 4 ሐሙስ — ፊልጵስዩስ 2፥1-11

1. በፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ምን ስሕተት ነበር (ቍ.1-4፤ 1፥27)?
2. ይህን ለማረም ጳውሎስ ያቀረበውን ምክንያትና ትእዛዝ ዘርዝር (1-5)።
3. ከክርስቲያኖች ጋር አንድነትህን ለማጠንከር ምን ማድረግ አለብህ?
4. * እግዚአብሔር ወልድ በመስቀል ውርደት ከክብር ወደ ክብር ሲሸጋገር፥ ሀ) ራሱን ዝቅ ሲያደርግ በምን ደረጃዎች አለፈ (6-8)? ለ) እግዚአብሔር በምን ደረጃዎች ከፍ ከፍ አደረገው (9-11)?
5. ራስህን ዝቅ ማድረግህ፥ ሀ) ከክርስቲያን ጉብረትህ፥ ለ) እግዚአብሔርን ከፍ ከማድረግህ ጋር እንዴት ይያያዛል?

ቍ.6 በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር (የመለኮት ባሕርይ አለው)፤ «መልክ» የሚለው ቃል የሚታየውን ሲያመለክት፥ የሚታየው ደግሞ የውስጡን፥ ማለትም የማይታየውን ባሕርይ ስለሚገልጥ፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ፍጹም አምላክ መሆንና በመለኮት ባሕርይ ሙላት ላይ ያተኮራል፤ እንዲሁም የባሪያን መልክ ይዞ በሰው ምሳሌ ሲኖር ጌታችን ታዛዥ ሆኖ ፍጹም ሰው መሆኑን ያመለክታል (7)።

መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም (አንደያዘ መትረት አልፈለገም)፤ ተወልድ አምላክነት የባሕርይ መሆኑን ሲያመለክት፥ ወልድ በራሱ ፈቃድ ዝቅ ብሎ መገኘቱን ያሳያል፤ ዕብ.10፥5-10።

ቍ.8 ራሱን ባዶ አደረገ (ራሱን ዝቅ አደረገ)፤ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጠው ወልድ ሰው በሆነ ጊዜ ዓለም ሳይፈጠር ከአብ ጋር በነበረው መለኮታዊ ክብር አልተጠቀመም እንጂ የመለኮት ባሕርያት (እውቀት፥ ኃይል ... ወዘተ) አልተለዩትም፤ ዮሐ.17፥5።

ሳምንት 4 ዓርብ — ፊልጵስዩስ 2፥12-18

1. ይህ አንቀጽ ከፊተኛው ጋር እንዴት ይገናኛል?
2. ክርስቲያን መዳኑን በዕለታዊው አካሔዱ ሲፈጽም (በተለይ አንድነት ከሌሎች ጋር ሲከታተል)፥ ሀ) የእርሱ ፈንታ፥ ለ) የእግዚአብሔር ፈንታ ምንድን ነው (12-13)?
3. ክርስቲያን መዳኑን በዓለም ፊት እንዴት ማሳየት ይገባዋል?
4. ጳውሎስ ለአንባቢዎቹ በአርአያነት ራሱን እንዴት ያቀርባል?

5. ከዚህ ምንባብ የተነሣ መዳንህን በተሻለ ረገድ ለመፈጸም ምን ማድረግ ትችላለህ?

ቍ.12 የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ፤ ሰው በክርስቶስ ሲያምን ይድናል፥ ከዚያም በኋላ በደኅንነቱ መሠረት አካሔዱን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ አድርጎ መኖኑን በማሳየት ይፈጽመዋል።

ቍ.13 በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና፤ ክርስቲያን ይታዘዛል፥ ለሚሠራውም ሁሉ ጎላፊና ተጠያቂ ሲሆን፥ መጀመሪያ ሲያምን በኋላም ለመልካም ነገር ሁሉ ፈቃደኛነቱና ታዛዥነቱ የሚመነጨው እግዚአብሔር በልቡናው በሚያሳድረው መንፈስ ነው፤ 1፥6፡29።

ቍ.17 ሕይወቴ እንኳ ቢፈስ፤ የመጠጥ ቍርባን በዕለታዊ በግ መሥዋዕት ላይ እንደተጨመረ ሁሉ፥ አስፈላጊ ከሆነ የጳውሎስ ሕይወት በፊልጵስዩስ ሰዎች እምነት፥ መሥዋዕትና አገልግሎት ላይ ቢጨመር እንደ ደስታ ሊቈጥረው ይችል ነበር፤ ዘኍ.28፥7-8።

ሳምንት 4 ቅዳሜ — ፊልጵስዩስ 2፥19-30

1. ጳውሎስ፥ ሀ) በጢሞቴዎስ፥ ለ) በአፍሮዲጡ እንዴት ሊጠቀም አሰበ?
2. ከዚህ ምንባብ ስለ፥ ሀ) ጢሞቴዎስ፥ ለ) አፍሮዲጡ (4፥18)፥ ሐ) ጳውሎስ ምን ትማራለህ?
3. እንደነዚህ ያሉ ሰዎችን ታውቃለህን? እንዴት ታከብራቸዋለህ?
4. በሕይወትህ የራስህን ወይስ የክርስቶስ ኢየሱስን ፈቃድ ትፈጽማለህ (21)?

ቍ.22 ልጅ ለአባቱ እንደሚያገለግል፤ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ያሳመነ ይመስላል፤ 1ቆሮ.4፥17፤ 2ጢሞ.1፥2።

ሳምንት 5 እሑድ — መዝሙር 56(57)

መግቢያ፤ ዳዊት በዋሻ ተደብቆ ለሳኦል እንደራራለት በ1ኛ ሳሙ.24 ተጽፎአል፤ ይህ መዝሙር እዚያ ዳዊት በነበረበት ጊዜ ለእግዚአብሔር ያቀረበው ጸሎት ነው።

1. ዳዊት በአደጋ ላይ ሳለ ስለ እግዚአብሔር እንዴት አሰበ (ቍ.1-2)?
2. ሀ) ስለ አስቸጋሪ ሁኔታው ምን ገለጠ (4፥6)? ለ) በዚያ ሁኔታ ላይ እያለ ዋና ፍላጐቱ ምን ነበር (5፥11)?
3. ዳዊት፤ «ልቤ ጨካኝ ነው» (በሙሉ ልብ እተማመናለሁ) ብሎ ሊመሰክር ወደማይናወጥ የልብ ሰላም በምን ደረጃዎች አልፎ ደረሰ (1-6)?
4. እምነቱ በቍ.7-11 በምን ይታያል?
5. አንተ በአደገኛ ሁኔታ ላይ ስትገኝ ከዚህ መዝሙር ምን ጠቃሚ ትምህርት ትማራለህ?

አታጥፋ፤ የዜማው ስም ይመስላል።

ሳምንት 5 ሰኞ — ፊልጵስዩስ 3፥1-11

መግቢያ፤ ሐዋርያው ለጢሞቴዎስና ለአፍሮዲጡ ከመሰከረ በኋላ ስለ ፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን አዲስ ነገር የደረሰው ይመስላል፤ በመልእክቱም ከባድ ማስጠንቀቂያ ጨመረ።

1. የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ከምን መጠበቅ ነበረባት (ቍ.2)?
2. በእውነት የተገረዘ ሰው ምስት ምልክቶች ምንድን ናቸው (3)?
3. ጳውሎስ በምን ሥጋዊ ነገሮች ሊመካ ይችል ነበር (4-6)?
4. እነዚህን ነገሮች እንደ ጉዳትና እንደ ጉድፍ ለምን ቈጠራቸው (7-11)?
5. የሃይማኖት ሰዎች ዛሬ በምን ሥጋዊ ነገሮች ይመካሉ?
6. አንተ እንደ ረብና እንደ ጉዳት የምትቈጥረው ምን አለ? ለምን?

ቍ.2 ውሾች፤ አይሁድ ያልተገረዙትን አሕዛብ እንደ ውሾች ይቈጥሩአቸው ነበርና፥ ጳውሎስ አሕዛብ እንዲድኑ ማዘዙት ያስፈጋቸዋል የሚሉትን የአይሁድን ወግ አጥባቂዎች የተለመደ ስድብና ከባድ ምጸት ተጠቅሞ ጠባያቸውን ገለጠ፤ ሐ.ሥ.15፥5፤ ገላ.5፥2-3፤ 2ጴጥ.2፥22፤ ራእ.22፥15።

ቍ.3 በሥጋም የማንታመን፤ ይህ በማዘዙት ወይም በሰው በሚሠራ በማናቸውም ሌላ ነገር ለመዳን ወይም እግዚአብሔርን ለማስደሰት የሚደረገውን ያመለክታል።

ቍ.5 ዕብራዊ፤ በአዲስ ኪዳን ቃሉ በግሪክ ዓለም ተጽእኖ ያልተለመጡትን አይሁድ፥ የጥንቱን የእስራኤል ቋንቋም ዕብራይስጥን የሚጠቀምበትን ሊያመለክት ይችላል፤ 2ቆር.11፥22።

ፈሪሳዊ፤ ሕግን በጥብቅ የተከታተለ የአይሁድ ወገን ሰም።

ቍ.11 በሀገልኛ፤ ጥርጥርን ሳይሆን ከባድ ምኞትን ያሳያል።

ሳምንት 5 ማክሰኞ — ፊልጵስዩስ 3፥12-16

1. ጳውሎስ፥ ሀ)ያገኘው፥ ለ)ያላገኘው ምን ነበር (1፥21፤ 3፥10-14)?
2. ጳውሎስ ይሆን ተረድቶ ምን ያደርግ ነበር (ቍ.12-14)?
3. ጳውሎስ ፍጹም፥ ሀ) ለመሆኑ (12)፥ ለ) ላለመሆኑ (15) አብራራ።
4. አንዳንድ ሰዎች በእካሄዳቸው ወይም በቃላቸው ወደ መንፈሳዊ ግብ እንደደረሱ መቍጠራቸውን ሲገልጡ አይተሃልን?
5. የአንተን መንፈሳዊ የዕድገት ደረጃ ከጳውሎስ ጋር አነጻጽር።

ቍ.15 ፍጹማን የሆንን (በመንፈሳዊ ሕይወት የጠነከርን)፤ በመንፈስ የበሰለ ሰው የጳውሎስን አስተሳሰብ ይዞ በፊቱ ያለውን ለመያዝ እጁን እየዘረጋ ይፈጥናል፤ 1ቆር.2፥6፤ ዕብ.5፥14።

ሳምንት 5 ረቡዕ — ፊልጵስዩስ 3፥17-21

1. ክርስቲያን ምን ዓይነት ሰውን መመልከት ይገባዋል (ቍ.17)?
2. ክርስቲያኖች ሃን እያሉ በሥጋ የሚመላለሱትን ሰዎች ጠባይ አብራራ (18-19)።

3. የእውነተኛ ክርስቲያናችን ሁኔታ ግለጥ (20)።

4. ጌታችን ሲመጣ ምን ያደርጋል (20-21)? በምን አኳኋን?


5. አንተ ሥጋህን በምን አኳኋን ታስገዛዋለህ? ለምን?

ቍ.18-19 3፥2ና ማስታወሻ ተመ.።

ቍ.20 አገራችን በሰማይ ነውና (የመንግሥተ ሰማይ ዜጎች ነን)፤ የፊልጵስዩስ ከተማ ነዋሪዎች በሙሉ የርም መቤት ስለ ነበራቸው በዜግነታቸው ይመኩ ነበርና ለጳውሎስ ትምህርት ምሳሌ ሆኑ።

ሳምንት 5 ሐሙስ

ፊልጵስዩስ 4፥1-7



1. በጌታ መቆም ምን ማለት ነው (3፥20-21፤ 4፥1)?

2. ሀ) ኤዎድያንና ሲንጤኪን እንዴት ያሉ ሴቶች ነበሩ? ለ) አለመስማማታቸውን ለማስወገድ መፍትሔው ምን ነበር (ቍ.2-3፤ 1፥27፤ 2፥1-5)? ሐ) የማይስማሙ አማኞች እንዲታረቁ ምን ታደርጋለህ?

3. የእግዚአብሔር ሰላም በልቡ እንዲገዛ ክርስቲያን ምን ማድረግ አለበት (4-7)?

4. ሀ) ምስጋና፥ ለ) ጭንቀት በሕይወትህ ምን ሰፍራ አላቸው? ለምን?

ቍ.1 አክሊል፤ በጌታ ለሚሥራ ሁሉ የታ አለው 1ቆሮ.15፥58፤ 1ተሰ.2፥19፤ ራእ.3፥11።

ቍ.3 በሕይወት መጽሐፍ፤ ዘጸ.32፥32፤ ሉቃ.10፥20፤ ራእ.13፥8፤ 20፥12፥15።

ቍ.6 በነገር ሁሉ...አትጨነቁ፤ መዝ.54(55)፥22፤ 1ጴጥ.5፥7።

ሳምንት 5 ዓርብ — ፊልጵስዩስ 4፥8-13

1. የእግዚአብሔር ሰላም በልቡ እንዲሠለጥን ክርስቲያን ምን ሌላ ነገር፥ ሀ) ማሰብ፥ ለ) ማድረግ አለበት (ቊ.8-9)?
2. ሐሰተኛ፥ ሰውን የማያከብር፥ ትክክለኛነት የሌለበት፥ ንጹህ ያልሆነ ወይም እነዚህን የመሰለ ሌላ የማይገባና የልብ ሰላምን የሚያደፈርስ ሐሳብ ሲኖርህ ምን ታደርጋለህ? ለምን?
3. ጳውሎስ አሁን ለምን ተደሰተ (10-13)?
4. ጳውሎስ ምን ተምሮ ነበር? ከነዚህ ሁኔታዎች በተለይ አስቸጋሪ ሆኖ ያገኘኸው የትኛው ነው? ለምን?
5.* ቊ.9ን ከ1ቆሮ.4፥16፤ 11፥1፤ 1ተሰ.1፥6፤ 1ጢሞ.4፥12-16፤ 1ጴጥ.5፥1-3 ጋር፥ ከምታውቀው ዋና መንፈሳዊ መሪህ ጋርና፥ ከሕይወትህ ጋር አስተያይ።

ሳምንት 5 ትዳጌ — ፊልጵስዩስ 4፥14-23

1. የፊልጵስዩስ ቤተ ክርስቲያን ጳውሎስን እንዴት ረድታ ነበር (ቊ.14-16)?
2. አሁን ስጦታቸውን በመቀበሉ ምን አሰበ (17-20)?
3. በስጦታ ላይ የእግዚአብሔር በረከት እንዴት ይገኛል?
4. ከቊ.10-20 ስለ ስጦታ፥ ሀ) መስጠት፥ ለ) መቀበል ምን ተምረሃል?
5. ስለ ጉብረት ከቊ.21-23 ምን ትማራለህ?

ቊ.17 ፍሬ፤ ማቴ.6፥20-21፤ ሉቃ.16፥9፤ ገላ.5፥22።

ቊ.18 የመዓዛ ሽታና የተወደደ መሥዋዕት፤ አባባሉ የብሉይ ኪዳንን መሥዋዕቶች ያሳስባል (ዘፍ.8፥20-21)፤ በክርስቶስ ስም ለሰው የሚሰጥ መባ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል፤ ዕብ.13፥16።

ሳምንት 6 እሑድ — መዝሙር 57(58)

1. ዳዊት ከፉ ገዢዎችን ስለ ምን ይወትሳቸዋል (ቊ.1-2)?
2. ለምን እንደዚህ ያደርጋሉ (3-5)?
3. ዳዊት የእግዚአብሔርን ፍርድ በምን ይመስለዋል (6-9)? ተስፋው ወይም ልመናው ምንድን ነው?
4. ጻድቅ ፍርድን ሲያይ ምን ያደርጋል (10-11)?
5. ትክክለኛ ፍርድ ባይገኝ ይህ መዝሙር ጸሎትህን እንዴት ይረዳል?

አታጥፋ፤ የመዝ.56(57)ን ማስታወሻ ተመ.።

ቊ.4 እንደ ምድር አውሬም ጀርባ የተደረጎ ነው (እንደ ደንቆር እፉኝትም ጀርአቸውን ያቀናሉ)፤ አባባ በተፈጥሮው ስለማይሰማ፥ አፍዛዙ በዋሽንት እንቅስቃሴ እንጂ በድምፅ አያፈዘውም።

ቁ.10 ጓድት፤ በዚህ መዝሙር ሐሳብ በሕሰት የተረረደበትን የእግዚአብሔር ሰው ያመለክታል።

መጽሐፈ ሩት

«መጽሐፈ ሩት» ባሉቻቸው የሞቱባቸውን የሦስት ሴቶች ታሪክ ይተርካል። እንዲቷ እስራኤላዊ ስትሆን ሁለቱ ለእስራኤል ሕዝብ ባዕድ ከሆነ ከሞዓብ ወገን ነበሩ። ከሦስቱ ሴቶች ሩት፥ ለአማትዋ ለአገራዊ ታማኝነት በማሳየትዋና የዳዊት ቅድመ አያት በመሆንዋ የታወቀች ሆነች።

«መጽሐፈ መሳፍንት» እግዚአብሔር በግይታዘዘው ሕዝቡ ላይ ፍርድን እንዴት እንዳመጣ ሲተርክ፥ «መጽሐፈ ሩት» በዚያ ዘመን እንኳን እግዚአብሔር ለሚታመንበት ቸርነቱን፥ እንዲሁም የሌላ ወገን ሰዎችን ለመባረክ ማቀዱን ያሳያል።

ሳምንት 6 ሰኞ — ሩት 1፥1-15



1. የኑኃሚን ቤተሰብ ባዕድ አምልኮ ወዳለበት ወደ ሞዓብ አገር በመሄዱ አስተሳሰቡ እንዴት ተለወጠ (ቁ. 1-4፤ ዘዳ. 23፥3-4)?
2. የሦስቱን ሴቶች ሐዘን ገምት (1-5)።
3. ኑኃሚን (ናዖሚ) ምራቶችዋን እንዴት መከረቻቸው? ለምን (6-13)?
4. የእግዚአብሔር እጅ በአንተ ላይ ሲደርስ አብረውህ ስላሉት ምን ይሰማሃል (13)?
5. የዖርፋን ጠባይና ውሳኔ አብራራ (6-15)።

ሳምንት 6 ማክሰኞ — ሩት 1፥14-22

1. ሩት ከኃብኞ በላይ ምን ቈጠረች (ቁ. 14-18)?
2. ታላቅ ውሳኔ ስታደርግ ከሁሉ በላይ የሚገፋፋህ ምንድን ነው?

3. በኑኃሚን አመካከር ምን ጥበብ ይታይሃል (11-18)?

4. የቤተልሔም ሰዎች በኑኃሚን ያዩትን ለውጥ ገምት (19-21)።

5. የኑኃሚን አስተሳሰብ ስለ እግዚአብሔር ትክክለኛ ነበርን? ለምን?

6. አንተ «ሙላት» ወይም «ባዶነት» መቼ ይሰማሃል? ለምን?

ቍ.17 በዚያም እተበራለሁ፤ በብሉይ ኪዳን ዘመን የመቃብር ስፍራ እንደ ታላቅ ነገር ይቈጠር ነበርና፥ ይህ ሐረግ የሩትን እምነት ያብራራል፤ ዘፍ.47፥30፤ 50፥25።

ቍ.20 ግራ...ኑኃሚን፤ በዕብራይስጥ «መራራ» እና «ደስታዬ» ግለት ነው።

ቍ.22 የገብስም መከር በተጀመረ ጊዜ፤ ድሆች ምንጥብ ለማግኘት በሚችሉበት ጊዜ እግዚአብሔር ወደ ቤተልሔም እደረሳቸውና ተስፋ ማግኘት ጀመሩ (ም.2)።

ሳምንት 6 ረቡዕ ሩት 2

መግቢያ፤ አሚጆች የመከሩን ታርሚያ ለድሆች እንዲተው በሕግ ታዘዙ (ዘሌ.23፥22፤ ዘዳ.24፥19-22)።

1. ሩት ለራስዋና ለአማትዋ አስፈላጊውን ለማግኘት ምን አደረገች?

2. ቦዔዝ ምን ዕድል ሰጣት? ለምን?

3. በአገርህ የድሆች ሙብት እንዴት ነው? በቂ ነውን?

4. ለሩት በተደረገው ምክንያት የኑኃሚን ሐሳብ ስለ እግዚአብሔር እንዴት ተለወጠ (ቍ.20ን ከ1፥13፡ 20-21 ጋር አነጻጽር)?

5. አንድ ሰው ልዩ አስተያየት ሲያደርግልህ ምን ታደርጋለህ?

ቍ.17 ኢፍ፤ አሥር ኪሎ ያህል።

ቍ.20 ሊቤዠን ከሚችሉት አንዱ ነው፤ ሰው ልጅ ሳይኖረው ቢሞት ወንድሙ ወይም ወንድም ከሌለው የቅርብ ዘመዱ የሚቤዥን ሚስት እንዲያገባ በሕግ ታዘዘ (ዘዳ.25፥5-10)። ደግሞም ርስት ከጪተ ሰብ እንዳይጠፋ የቅርብ ዘመዱ የድሀውን መሬት እንዲቤዥ ታዘዘ (ዘሌ.25፥25፡48-49)። ኢዮብ ይህን ሐሳብ ተከትሎ እግዚአብሔር እንደሚቤዠው ተናገረ (19፥25)።

ሳምንት 6 ሐሙስ ሩት 3

1. ሀ) ኑኃሚን ለሩት አሁን ምን አደረገች (ቍ.1-4ን ከ1፥11-13 ጋር አነጻጽር)? ለ) ይህን ለማድረግ የዘገየችበት ምክንያት ምን ይመስልሃል?

2. ሩት ወደ አውድማው ስትቀርብ ፍርሃትዋንና ተስፋዋን ገምት (5-9)።

3. ከቍ.10-15 ስለ ቦዔዝ ጠባይ ምን ታስተውላለህ?

4. ሰዎች በሥጋ ሆነ በጭንቀት መንፈስ ወደ አንተ ቢቀርቡ በምን አኳኋን ትረዳቸዋለህ?

5.* ይህ ታሪክ ሰ.ኤ.3፥22-26፡31-33፤ ናሆም 1፥7ና ሮም 8፥28ን እንዴት ያብራራል?

ቍ.9 ልብስህን በባሪያህ ላይ ዘርጋ፤ ሰው ዘመዱ እንዲጠብቀውና እንዲቤዠው የዚያ ዘመን የሕጋዊ አቤቱታ ደንብ ነበር፤ ይህንም ሲያደርግ ዘመዱ ለወጪው ሁሉ ኀላፊ ነበረ፤ 4፥4-6፤ ገላ.3፥13-14።

ቁ.10-11 ጉበዛዝትን አልተከተልሽም፤ ሩት ወደ እርሱ በሙትረብዋ ቦዔዝ እድለኛ መሆኑ ተሰማው፤ ይህ ዓይነት ስሜት በጥሩ ጋብቻ ውስጥ በሁለቱም ይገኛል።

ሳምንት 6 ዓርብ — ሩት 4፥1-12

1. ቦዔዝ፥ ሀ) የኑኃሚንን የርስት ድርሻ በመቤዠት፥ ለ) ሩትን በማግባት ከራሱ ልጆች ርስት ምን ያህል ወጪ ሊያወጣ ይችል ነበር (2፥1፤ የ2፥20ን ግለታወሻ ተመ.)?
2. ቦዔዝ ጉዳዩን እንዴት አስረዳመ (ቁ.1-11)?
3. የከተማይቱ ሽማግሌዎች ቦዔዝንና ሩትን እንዴት ባረኩ (11-12)?
4. በዘመዶችህ መካከል ጎላፊነትህን በምን አኳኋን ትወጣለህ?

ቁ.12 ትዕግር፤ የእርሷ ግንኙነት ከይሁዳ ጋር ተገቢ አልነበረም (ዘፍ.38)፤ እስራኤላዊ ደግሞ ከሞዓባዊት ጋር መጋባት ነውር ነበር (ዘዳ.23፥3-4)፤ ሆኖም እግዚአብሔር ከእነዚህ ዓይነት ሁኔታዎች እንኳን በረከት ሊያመጣ ይችላል።

ሳምንት 6 ቅዳሜ — ሩት 4፥13-22

1. አሁን የኑኃሚንንና የሩትን ሁኔታ በፊት ከነበራቸው ሁኔታ ጋር አነጻጽር (ቁ.13-16)
2. እግዚአብሔር ምን ምን ጉድለት ሞላላቸው?
3. በሕይወትህ ምን ጉድለት አለ? ይህንስ ለእግዚአብሔር ትገልጠዋለህ?
4. ሞዓባዊቷ ሩት በዳዊትና በክርስቶስ ትውልድ ሐረግ እንዴት ገባች (18-22፤ ማቴ 1፥2-6)? ይህስ ስለ እግዚአብሔር ዕቅድ ምን ያሳይሃል (ዘዳ.23፥ 3-4)?
5. * ከሦስቱ ሴቶች ታሪክ እምነት፥ ታማኝነትና ትዕግሥት በመጨረሻ የእግዚአብሔርን በረከት እንዴት እንደሚያስገኙ ግለጥ።

የማርቆስ ወንጌል

ሳምንት 7 እሑድ — ማርቆስ 1፥1-8

መግቢያ፤ ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ ከእናቱ ጋር በኢየሩሳሌም የኖረ፥ የበርናባስ ዘመድ፥ የጳውሎስና የበርናባስ ወንጌላዊ ጓደኛ፥ በኋላም ከጴጥሮስ ጋር የሠራ አገልጋይ እንደነበረ በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት እናገኛለን። እንደ ጥንት የቤተ ክርስቲያን ትውፊት ማርቆስ ብዙ ጊዜ የጴጥሮስን ስብከት በመስማቱ፥ ለተሰደዱት ሮማውያን ምእመናን ወንጌልን ለመጻፍ በታ። ማርቆስ የኢየሱስን ልደትና እድገት ባለመተረኩ፥ ብሉይ ኪዳንን ብዙ ባለመጥቀሱና የኢየሱስን ትምህርት በሰፊው ባለመመዝገቡ ወንጌሉ እንደ ማቴዎስና እንደ ሉቃስ ወንጌል ረጅም አይደለም። ማርቆስ በኢየሱስ አድራጎት ላይ ያተኮራል፥ ብዙ ጊዜ ኢየሱስ «ወዲያውም» በማለቱ የኢየሱስን አገልግሎት ያብራራል አገልግሎቱም በሞቱ የተረዳመ መሆኑን ያሳያል (10፥45)።

1. ስለ መጥምቁ ዮሐንስና ስለ አገልግሎቱ ቢያንስ አምስት ነጥቦችን ዘርዝር።

2. ዮሐንስ በራሱና በሚመጣው መካከል ስላለው ልዩነት በምን ላይ አተኩረ?

3. ጓደኞችህንና ቤተ ሰብህን ለጌታ ማዘጋጀት እንዴት ትችላለህ?

ቍ.4 ጥምቀት፤ የዮሐንስ ዓላማ ሰዎችን ለክርስቶስ መምጣት ማዘጋጀት ነበረ።

ሳምንት 7 ሰኞ — ማርቆስ 1፥9-20

1. በጥምቀት ጊዜ፥ ሀ) አብ፥ ለ) ወልድ (ኢየሱስ ክርስቶስ)፥ ሐ) መንፈስ ቅዱስ ምን አደረጉ?

2. ኢየሱስ ሲፈተን በምን አካኋን ነበረ?

3.* ኢየሱስ፥ ሀ) በመጠመቁ፥ ለ) በመፈተኑ ለአገልግሎቱ እንዴት ተዘጋጀ?

4. ቍ.14-20 ስለ እግዚአብሔር መንግሥት፥ ሀ) ሁኔታ፥ ለ) መነሻ፥ ሐ) አባላት፥ መ) ሠራተኞች ምን ይገልጣል?

5. አንተ፥ ሀ) የመንግሥቱ አባል፥ ለ) ሰውን አጥማጅ ለመሆን ምን ያስፈልግሃል?

ቍ.9 ከገሊላ ናዝሬት መጥቶ፤ ኢየሱስ አገሩን ትቶ ወጣ፤ ወደዚያም ተመልሶ እንደገና አልኖረም።

ቍ.11 የምወድህ ልጄ፤ አብ የባሕርይ ልጁ መሆኑን አረጋገጠለት።

ቍ.12 ምድረ በዳ፤ የእስራኤል ሕዝብ በሲና ምድረ በዳ እንደተፈተኑ ሁሉ፥ ኢየሱስ በይሁዳ ምድረ በዳ ተፈተነ፤ መዝ.94(95)፥8።

ቍ.13 ከአራዊትም ጋር ነበረ ...፤ ኢየሱስ ይህን መከራ ያየው በመሆኑ ለሚሰደዱት መጽናኛ ነው፤ 1ቆሮ.15፥32፤ ዕብ.2፥18፤4፥15።

ቍ.14-15 ዮሐንስ ከመታሰሩ በፊት ኢየሱስ በገሊላና በይሁዳ ለጥቂት ወራት ሥራውን ጀምሮ ነበር ዮሐ.1፥29-4፥54።

የእግዚአብሔር መንግሥት መጋቤል፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በመምጣቱ የእግዚአብሔርን መንግሥት ማቋቋም ጀመረ፥ መንግሥቱም በምድራዊ ድምበር ሳይወሰን ሰዎች ሕጉን በልባቸው ተቀብለው ሲኖሩበት የሚገለጥ ነው፥ አይሁድ ግን በሮም ቅኝ ግዛትነት ለብዙ ዓመታት በመኖራቸው ነጻነታቸውን የሚያስመልሰላቸውንና ኃያል መንግሥትን የሚያቋቁምላቸውን መሲሕ ይጠብቁ ነበር።

የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች፤ መንግሥት የሚቋቋመው ንጉሡ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጣና ተቀባይነትን ሲያገኝ ብቻ ነው።

ሳምንት 7 ማክሰኞ — ማርቆስ 1፥21-34

መገሢያ፤ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት መቅረብ ለመግለጥ ሲመጣ ማናቸውንም ክፉ ኃይልና ሥልጣን በማስወገዱ የመልእክቱን እውነተኛነት አረጋገጠ።

1. ሕዝቡ በኢየሱስ ትምህርት ለምን ተገረሙ (ቍ.21-22)?

2. የኢየሱስ ሥልጣን በምን ተገለጠ (23-28)?

3. ቍ.29-31 ስለ ኢየሱስ ምን ያሳያል?

4. ኢየሱስ ምን ዓይነት ሰዎችን ከችግራቸው አዳነ (32-34)?

5.* ምንባቡ ስለ አጋንንት ምን ይገልጣል?

6. የእግዚአብሔር ኃይል፥ ሀ) በሌሎች፥ ለ) በራስህ ሕይወት ሲገለጥ ምን ታደርጋለህ?

ቍ.21 ትፍርናሆም፤ በገሊላ የኢየሱስ አገልግሎት ማእከል ሆነ። ካርታ ተመ.።

ምኵራብ፤ የአይሁድ የጸሎትና ማኅበራዊ ጉዳይ መሰብሰቢያ ቤት።

ቍ.23 ርኵስ መንፈስ፤ ሰውን የሚያስጨንቅና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዳይኖረው የሚከለክል ጋኔን፥ የሰይጣን መልእክ።

ቍ.32 በመሸ ጊዜ፤ እንደ ወጋቸው አይሁድ ሰንበት እስኪያልፍ ድረስ ብዙ መንገድ አይሒዱም ወይም አይሸኩም ነበር፤ ሐ.ሥ.1፥12።

ሳምንት 7 ረቡዕ — ማርቆስ 1፥35-45

1.* ይህ ምንባብ ስለ ኢየሱስ፥ ሀ) ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት፥ ለ) አገልግሎት ዓላማ፥ ሐ) ለተናቁት ርኅራኄ፥ መ) ሕግን ማክበር ምን ይገልጣል?

2. ሀ) ኢየሱስ ለምጻሙን እንዳይናገር የከለከለበት፥ ለ) ለምጻሙ ያልታዘዘበት ምክንያት ምን ይመስልሃል?

3. የለምጻሙ አለመታዘዝ ውጤት ምን ነበር?

4. ኢየሱስ ሕይወቱን የመራበትን ዘዴ ከራስህ ጋር አስተያይ (35፡45)።

ቍ.38 ስለዚህ ወጥቼአለሁ፤ ቍ.14-15 ተመ.።

ቍ.40 ለምጻም፤ በቆዳ ላይ የሚታይ ማናቸውም ዓይነት ተላላፊ በሽታ ያለበት፤ ሌሎች በሽተኞች እንዲፈወሱ፥ ለምጻሞች እንዲነጹ ጠየቁ፥ ምክንያቱም በሕግ መሠረት እንደ ርኵስ ተቈጥረው ከከተማና ከጉባኤተሰብ ውጭ ይኖሩ ነበር፤ ዘሌ.13፥45-46።

ቍ.41 ዳሰሰው፤ ኢየሱስ እንደማይረክስ አውቆ ሳይፈራ ርኅራኄውን አሳየ።

ቍ.45 ኢየሱስ መንግሥቱን ማስፋፋት እንጂ ተአምራትን በማድረግ ሰዎችን መሳብ አልፈለገም።

ሳምንት 7 ሐሙስ — ማርቆስ 2፥1-12

1.* በቤቱ ውስጥ እነማን እንደነበሩ ገምት (ቍ.1-6፤1፥21-34)። ከነበሩት ሰዎች መካከል ራስህን ከማን ጋር አንድ ማድረግ ይቀልሃል? ከአራቱ ሰዎች፥ ከሽባው፥ ከጻፎች (ከሕግ መምህራን) ወይስ ከሌሎች ጋር? ለምን?

2. አንተ እዚያ ብትገኝ ኖሮ በተለይ ልብህን የሚነካው ነገር ምን ይመስልሃል?

3. ኢየሱስ ሽባውን ሲመለከት በምን ላይ አተኩረ?

4. የጻፎቹ ስሕተት ምን ነበር?

5. ይህ ተአምር ስለ ኢየሱስ፥ ሀ) ማንነት፥ ለ) ሥልጣን፥ ሐ) ተልእኮ ምን ይገልጣል?

6. ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለማቅረብ ስትሞክር፥ ሀ) ዓላማህ ምንድን ነው? ለ) ምን እንቅፋት የሚያጋጥምህ ይመስልሃል?

ዮ.5 ኃጢአትህ ተሰረየችልህ፤ አይሁድ የኃጢአት በሽታና ፈውስ እንደተያያዙ ያስቡ ነበር፤ መዝ.102(103)፥3።

ሳምንት 7 ዓርብ — ግርቶስ 2፥13-17

1. ሌዊ (ማቴዎስ) እምነቱን እንዴት ገለጠ (ማቴ.9፥9-10)?
2. ማቴዎስ ለአንተ በምን በኩል ምሳሌ ይሆናል?
3. በግብዣው ላይ እነማን ነበሩ?
4. ፈሪሳውያን የኢየሱስ አካሔድ ከትምህርቱ ጋር አለመስማማቱን እንዴት አሰቡ?
5. ኢየሱስ በመልሱ፥ ሀ) ተልእኮውን እንዴት አብራራ፥ ለ) ፈሪሳውያንን በስውር እንዴት ወቀሳቸው?
6. አንተ ምን ዓይነት ሰዎችን ለማሳመን ትሞክራለህ? «ኃጢአተኞች»ን ወይስ «ጻድቃን»ን? ለምን?

ሉ.15 ቀራጮች፤ ለሮም መንግሥት በመሥራታቸውና ከመጠን በላይ ቀረጥ በማስከፈል ለራሳቸው ሀብትን በመሰብሰባቸው እጅግ የተጠሉና የተነቀፉ ነበሩ።

ኃጢአተኞች፤ ቃሉ ሴተኛ አዳሪዎችን (ሉቃ.7፥37) ወይም ሕግንና የሽግግሌዎችን ወግ በቸልተኝነት የጣሱትን ሊያመለክት ይችላል፤ ማር.7፥5።

ሳምንት 7 ቅዳሜ — ግርቶስ 2፥18-28፤3፥1-6

1. ኢየሱስ ጾምን ከሕይወቱ ጋር እንዴት አገናኘው (2፥18-20)?
2. የኢየሱስ ትምህርት የአይሁድን ሥርዓት ሊያድስ ለምን አይችልም ነበር (2፥21-22)?
3. ወግና ልማድ በሕይወትህ ምን ስፍራ ይይዛሉ? የወንጌል እውቀት እንዴት ይለውጣቸዋል?
4. ሀ) ደቀ መዛሙርቱ፥ ለ) ኢየሱስ በሰንበት ቀን ምን አደረጉ (2፥23-3፥6)? ለምን?
5. የፈሪሳውያን ስሕተት ምን ነበር (2፥27-28)? ምንስ አደረጉ (3፥6)?
6. በሰንበት ቀን እንዴት ትጠቀማለህ? ክርስቶስ የእረፍትህ ጊዜ ጌታ ነውን?

2፥20 በዚያ ወራት ይጦማሉ፤ ዮሐ.16፥9-22 ተመ.።

2፥23 እሸት ይቀጥፉ ጀመር፤ ይህን ማድረግ በሕግ ተፈቀደ (ዘዳ.23፥25)፥ ፈሪሳውያን ግን ይህን እንደ ሥራ ቈጥረው በሰንበት እንዳይቀጠፍ ይከለክሉ ነበር (24)።

2፥25-26 ዳዊት...በተራበ ጊዜ፤ ኢየሱስ የሕግን ሥርዓት ከመጠበቅ ይልቅ የሰውን ችግር ማቃለል እንደሚበልጥ መግለጡ ከዚህ ታሪክ ይታያል።

3፥2 በሰንበት ይፈውሰው እንደሆን፤ ፈሪሳውያን በሰንበት የተፈቀደው የፈውስ ሥርዓት የሞት አደጋ ሲኖር ብቻ መሆኑን አስተማሩ።

3፥6 የሄሮድስ ወገን፤ በገሊላ አገረ ገዥ ዘንድ ተጽእኖ ማድረግ የቻሉ ታላላቅ ሰዎች።

ሳምንት 8 እሑድ — ማርቆስ 3፥7-19

መግቢያ፤ ማርቆስ ከዚህ በፊት አራት ዓመ አጥማጆችና አንድ ቀራጭ ለደቀ መዛሙርትነት መጠራታቸውን ጽፏል፥ አሁን እነርሱና ሌሎች ሰባት ሰዎች ለሐዋርያነት እንዴት እንደተሾሙ ይተርካል።

1. በዚህ ጊዜ ኢየሱስን ያዳመጡ ከየት መጡ? ለምን?
2. ኢየሱስ በዚህ ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ አሥራ ሁለቱን የለየበት ምክንያት ምን ይመስልሃል?
3. አገልግሎታቸውንና ሥልጣናቸውን ከኢየሱስ አገልግሎትና ሥልጣን ጋር አስተያይ (ቍ.14-15ን ከ9-10 ጋር)።
4. ለአገልግሎታቸው እንዲዘጋጁ መጀመሪያ ምን ያስፈልጋቸው ነበር (11)?
5. ከዚህ ምንባብ ስለ አገልግሎትህ ምን ትማራለህ?

ሳምንት 8 ሰኞ — ማርቆስ 3፥20-35

መግቢያ፤ ኢየሱስ ምንም እንኳ ብዙ ሰዎችን ቢፈውስ፥ አጋንንትን ቢያወጣና ቢያስተምርም ተቃውሞ እየበዛበት ሔደ፥ የራሱም ቤተሰብ ተልእኮውን አልተረዳም። ሆኖም የመንግሥቱን ሁኔታ በይበልጥ ለግብራራት ባለግስተዋላቸው ተጠቀመ።

1. ኢየሱስ ተልእኮውን እንዲተው ምን ተደረገ (ቍ.21-22)?
2. የኢየሱስን ሁለት «ቤተሰቦች» አነጻጽር (20-21፡31-35)።
3. ለሁለቱ ቤተሰቦችህ ኀላፊነትህን እንዴት ትወጣለህ?
4. ኢየሱስ ለጻፊዎቹ መልስ ሲሰጥ፥ ሀ) የሐሳባቸውን አለመያያዝ፥ ለ) የራሱን ሥልጣን፥ ሐ) ይቅርታ የማይደረግለትን ኃጢአት እንዴት አብራራ (23-29)?
5. አንድ ሰው «ይቅርታ የማይደረግለትን ኃጢአት ሠርቼአለሁ» ቢልህ እንዴት ትመክረዋለህ?

ቍ.22 ብሔልዘቡል፤ «የቤት ጌታ» ወይም በአሽሙር «የዝንብ ጌታ» ማለት ሲሆን ሰይጣንን ያመለክታል።


ቍ.29 በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚሳደብ ሁሉ...አይሰረይለትም፤ ጻፊዎች እንዳደረጉ ሁሉ ማንኛውም ሰው የእግዚአብሔርን ሥራ አይቶ ከሰይጣን ነው ብሎ ቢሳደብ ከእግዚአብሔር ጸጋ ፍጹም ወጥቶአልና ለእርሱ ተስፋ የለውም።

ሳምንት 8 ማክሰኞ — ማርቆስ 4፥1-20

መግቢያ፤ ኢየሱስ በብዙ ዓይነት ምሳሌ ያስተምር ነበር (2፥17-22)፥ አሁን ግን ከሃይማኖት መሪዎች አልከኝነት የተነሣ (3፥6፡22) በይፋ ሲያስተምር መተርጐም (ፍች) በሚያስፈልጋቸው ምሳሌዎች መጠቀም ጀመረ።

1. በምሳሌው ነገሮቹን ሁሉ ከነፍቻቸው ጐን ለጐን ጻፍ።

2. የኢየሱስ ትምህርት በብዙ አድማጮቹ ዘንድ ፍሬ ለምን አላፈራም?
3. የመንጌልን ስብከት ሰምረት በምን መሠረት ልንመዝን ይገባናል (ሮ.20)?
4. የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋት ምን ማድረግ አለብን?
5. የእግዚአብሔር ቃል በሕይወትህ ፍሬ እንዲያፈራ ምን እንትፋት አለ?
6.* ኢየሱስ በዚህ ዓይነት ምሳሌ ሲያስተምር ዓላማው ምን ነበር (10-13፡33-34)?



ዘሩ የእግዚአብሔር ቃል ነው

ሮ.11-12 በሮቂ ላሉት...፤ ሰው የክርስቶስ ተከታይ እስኪሆን ድረስ የእግዚአብሔርን ነገር ሊያስተውል አይችልም፤ ግቴ.7፡6፤ 1ቆሮ.2፡14-15።

ሳምንት 8 ረቡዕ — ማርቆስ 4፡21-34

መግቢያ፤ በአንድ ምሳሌ የነገሮቹ ፍች (ትርጉም) ባይሰጥህ፡ የምሳሌውን ዋና ሐሳብ ለመረዳት ሞክር እንጂ ለእያንዳንዱ ነገር ፍች ባትፈልግ ይሻላል።

1. ሰው የመንግሥቱን ቃል በምን አኳኋን መስማት አለበት (ሮ.21-25)? ለምን?
2. የመንጌል ቃል ከተዘራ በኋላ በግደግ ላይ ሲገኝ፡ ሀ) ምን ያህል ግውቅ፡ ለ) ምንስ ግድረግ እንችላለን (26-29)?
3. በእግዚአብሔር መንግሥት የአንድ ሥራ መጀመሪያና መጨረሻ እንዴት ይያያዛሉ (30-32)?
4. የእግዚአብሔር ቃል ራሱን የቻለ ሕይወት እንዳለው ካመንህ፡ በምን መንገድ በሰው ልብ ውስጥ ለመዝራት ትሞክራለህ?

ሳምንት 8 ሐሙስ — ማርቆስ 4፡35-41

መግቢያ፤ ይሆን ተአምር በይበልጥ እንድናስተውል፡ ሀ) ኢየሱስ ቀኑን ሁሉ በግስተግሩ ደክሞ እንደነበር፡ ለ) ከደቀ መዛሙርቱ ቢያንስ አራቱ ባሕሩን ያወቁ ዓሣ አጥማጆች እንደነበሩ፡ ሐ) አይሁድ እግዚአብሔር ብቻ ነፋስንና ማዕበልን መግዛቱን እንዳመኑ መገንዘብ ይረዳናል።

1. አንቀጹ ስለ ኢየሱስ፥ ሀ) ትስብእት (ሰው መሆን)፥ ለ) ሥልጣን፥ ሐ) ዓላማ ለደቀ መዛሙርት ምን ይገልጣል?
2. ደቀ መዛሙርቱ ምን አደረጉ? ለምን? ከተአምሩ በኋላስ ምን አሉ?
3. ስሕተታቸው ምን ነበር? በእምነታቸው ምን ጉድለት ነበር?
4. አልፎ አልፎ ለምን ትጨነቃለህ? ስሕተትህ ምንድን ነው?

ሳምንት 8 ዓርብ — ማርቆስ 5፥1-20

1. ከኢየሱስ ጋር ከመገናኘቱ በፊትና በኋላ የሰውዬውን ሁኔታ አነጻጽር።
2. ከምንባቡ ስለ አጋንንት፥ ሀ) እውቀት፥ ለ) ፍርሃት፥ ሐ) ምኞት፥ መ) ኃይል ምን ትማራለህ?
3. ኢየሱስ አጋንንት ወደ አሳሞች እንዲገቡ በመፍቀዱ ምን ታስተውላለህ?
4. ኢየሱስ ከአገራቸው እንዲወጣ ሰዎች ለምን ጠየቁት?
5. ኢየሱስ ሰውየው ከእርሱ ጋር እንዲሄድ ለምን አልፈቀደም?

ቍ.13 በባሕር ሰጠሙ፤ አጋንንት ከሰውየው እንደወጡ በዚህ በገሐድ ተገለጠ።

ሳምንት 8 ቅዳሜ — ማርቆስ 5፥21-43

1. ኢየሱስ፥ ሀ) ለሴቲቱ፥ ለ) ለኢያኢሮስ፥ ሐ) ለምስቱ ሐዋርያት፥ መ) ለለቀስተኞቹ፥ ሠ) ለልጅቱ፥ ምን አደረገ?
2. ለእያንዳንዱ አድራጎት ምን ምክንያት ነበረ?
3. ይህም ሁሉ ስለ ኢየሱስ ባሕርይና ሥልጣን ምን ይገልጣል?
4. ይህም ሁሉ እምነትህን እንዴት ያጸናል?

ቍ.25 ደም የሚፈሳት ሴት፤ በዚህ ሁኔታ «ርኵስ» ነበረችና በሕዝብ መካከል መገኘት የለባትም ነበር፤ ዘሌ.15፥19-25።

ቍ.39 ተኝታለች እንጂ አልሞተችም፤ ልጅቱ ሞታ ነበር (ሉቃ.8፥52-55)፥ ነገር ግን ኢየሱስ ሕይወት በመሆኑ ሥጋዊ ሞት የሰው ሕይወት መጨረሻ አለመሆኑ ላይ ያተኩረ ይመስላል፤ ዮሐ.11፥11-14፥25፤ 1ተሰ.4፥13-18።

ሳምንት 9 እሑድ — ማርቆስ 6፥1-13

1. ኢየሱስ አገሩን ከመልቀቁ በፊት ከናዝሬት ሰዎች ውዝግብ ስለ ሕይወቱ ምን ትረዳለህ (ቍ.1-3)?
2. የናዝሬት ሰዎች ስሕተትና ውጤት ምን ነበር(4-6)?
3. አንተ ሰዎችን ለማመን ምን ያስቸግርሃል?
4. ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ሲልክ የሰጣቸውን ትእዛዛት ዘርዝር(7-11)።
5. እነዚህ ትእዛዛት ስለ አሥራ ሁለቱ ተልእኮ ሁኔታ ምን ይገልጣሉ?
6. * የአሥራ ሁለቱን ተልእኮና ውጤት ከዛሬ ወንጌል ሰባኪዎች ሥራ ጋር አነጻጽር።

ቍ.5 ተአምር ሊያደርግ ምንም አልቻለም፤ ኢየሱስ ወሰን የሌለው ኃይል ነበረው፤ ነገር ግን ሰዎች ሲታወሙት ተአምር ቢሠራ ኖሮ ዋናውን የመንግሥቱን መልእክት አያስተውሉም ነበር።

ቍ.12 ንስሐ እንዲገቡ ሰበኩ፤ 1፥4፡14-15።

ሳምንት 9 ሰኞ — ማርቆስ 6፥14-29

1. ከዝናው የተነሣ ስለ ኢየሱስ ምን ሐሳብ ተገኘ (ቍ.14-16)?
2. የሄሮድስ ሐሳብ ስለ ዮሐንስ እንዴት ነበር (17-20፡26)?
3. ሄሮድያዳ ዮሐንስን ለማስገደል ምን አደረገች (19-28)?
4. ሄሮድስን ወደ መጥፎ ሕሊና ያደረሱትን እርምጃዎች በቅደም ተከተል ጻፍ።
5. ክፉ ጎሊና እንዳይኖርህ ምን ማድረግ ትችላለህ?

ቍ.18...አልተፈቀደም፤ ዘሌ.18፥16፤ 20፥21።
ቍ.22 የመንግሥቴ እኩሌታ ስንኳ ቢሆን፤ አስ.5፥3፡6።

ሳምንት 9 ማክሰኞ — ማርቆስ 6፥30-44

1. ኢየሱስ በሕይወቱ ለእረፍት የሰጠውን ስፍራ አንተ ትሰጣለህን (ቍ.30-32)?
2. ኢየሱስ ዕቅዱን ለመለወጥ ምን ገፋፋው(33-34)?
3. ሕዝቡ ሲመገብ፥ ሀ) የሐዋርያት፥ ለ) የኢየሱስ ድርሻ ምን ነበር?
4. በዚህ ተአምር አምላካዊ ኃይልና የሰው ሥርዓት እንዴት ተገናኙ?
5. የግይቻልህን ነገር ለማድረግ ሁኔታዎች ሲያስገድዱህ (37) ከዚህ ምንባብ ምን መመሪያ ታገኛለህ?

ቍ.34 እረኛ እንደሌላቸው በጎች፤ ዘኍ.27፥16-17፤ ሕዝ.34፥5።
ቍ.37 ዲናር፤ የቀን ሠራተኛ ዋጋ፤ ማቴ.20፥2።
ቍ.44 ወንዶቹ ...፤ ሴቶችና ልጆች አልተቈጠሩም።

ሳምንት 9 ረቡዕ — ማርቆስ 6፥45-56

መግቢያ፤ ብዙዎቹ የመንግሥቱን ሁኔታ ሳያስተውሉ ሊያነግሡት እንደፈለጉ ኢየሱስ አወቀ (ዮሐ.6፥15)።

1. 5000 ሰዎችን ከመገበ በኋላ ኢየሱስ ወዲያው ምን አደረገ (ቍ.45-46)? ለምን?
2. ሐዋርያት ከዚህ ረጅም የሥራ ቀን በኋላ ምን አጋጠማቸው (47-50)?
3. ኢየሱስ ከሐዋርያት ጋር በምን ሦስት የተለያዩ ስፍራዎችና ሁኔታዎች ላይ ነበር (46-51)?
4. ሀ) የበላይነቱን፥ ለ) ኀርነቱን እንዴት አሳያቸው (50-56)?
5. ሐዋርያት ለምን ተገረሙ?

6. ኢየሱስ «አይዞህ እኔ ነኝ፥ አትፍራ» በ
አቃለለልህ? ለምን አስፈላጊ ነበር?

ቍ.48 በአራተኛው ክፍል፤ ከሌሊቱ በ9ነኛና በ
ሊያልፋቸውም ይወድ ነበር፤ ኢየሱስ ፍላጎታች
ለመግባት አልፈለገም ነበር (ሉቃ.24፥28)።

ቍ.53 ጌንሴሬጥ፤ ከቅፍርናሆም በስተ ደቡብ በ

ሳምንት 9 ሐሙስ

መግቢያ፤ የአይሁድ ባለሥልጣና
እውነተኛውን ሃይማኖት እንደሚቃረን ግሳየ

1. ከዚህ ምንባብ ስለ አይሁድ ወግ ምን እ
2. ኢየሱስ «ግብዞች» ብሎ ለምን ወቀሳቸ
3. ግብዝነታቸውን ለግሳየት ምን ምሳሌ ሰ
4. ዛሬ ልጆች ወላጆቻቸውን እንዳይረ
እንደምታከብር በምን ይታያል?
5. ኢየሱስ የአይሁድን ወግ በምን መሠረት
6. ያንተ ቤተ ክርስቲያን ወግ፥ ባሕል
በእውነተኛ አምልኮ ላይ ተመሥርቶአል
አለን? ካለስ ምንድን ነው?

ሳምንት 9 ዓርብ

መግቢያ፤ የሙሴ ሕግ ሰው ልዩ ል
እንደዚሁም በተለያዩ ሌሎች ነገሮች ራሱን
ሁሉ ዓላማ እስራኤል ከሌሎች ሕዝቦች
በባሕላቸው እንዳይበከሉ ነበር። መሲሕ
ስለሚሰበክ፥ እነዚህ ትእዛዛት ጊዜአዊ
አልተረዱም ነበር። ኢየሱስም መሲሕ
ሥልጣን ነበረው (ሐ.ሥ.10፥15)።

1. ሰውን ሊያረክስ የማይችለው ምንድን ነ
2. ግናቸውም ዓይነት ምግብ አንተን ግር
3. ሰውን የሚያረክሰው ምን ዓይነት፥ ሀ
(20-23)?
4. በአንተ ዘንድ በተለይ ንጽሕናህን የሚያ
5. ኢየሱስ አሕዛብን እንደ ርኩስ ሕ
መንግሥቱ ሊያስገባቸው እንደወደደ እ
6. ከሴቲቱ እምነት፥ ንዝነዛና ጮሌነት ለ

ቍ.24 ጢሮስ...ሲዶና፤ ከእስራኤል አገር

ቍ.27 ለውችሉች፤ አይሁድ «ውሾች» ብለው አሕዛብን ይሰድቡ ነበር፤ «ቡችሎች» ነተረታ ባይሆንም የዝር ልዩነትን ያመለክታል።

ሳምንት 9 ቅዳሜ — ማርቆስ 7፥31-37፤ 8፥1-10

መግቢያ፤ ኢየሱስ ከእስራኤል አገር ውጭ በስተ ምሥራቅ ወደ ነበረው ወደ ገሊላ ባሕር ደረሰ። በዚያም ከገሊላ አገር ብቻ ሳይሆን ከእስራኤል አገር ውጭ የሚኖሩ ብዙ ሰዎች ሊሰሙት የመጡ ይመስላል።

1. ከኢየሱስ ምስት አድራጎቶች ሰውዬው ምን ሊያስተውል ይችል ነበር (8፥33-34)?
2. ሰዎቹ ምን ፈልገው ነበር? ምን እንዲያደርጉ ታዘዙ? ምንስ አደረጉ? ለምን (8፥31-37)?
3. ሰው ለሚቸገርበት ነገር ሁሉ ኢየሱስ መፍትሔ እንደሆነ ዛሬ እንዴት ማሳየት እንችላለን?
4. «አትንገሩ» (36) የሚለውን ትእዛዝ ከ5፥19 ጋር አነጻጽር።
5. * 8፥1-10ን ከ6፥33-44 ጋር ጐን ለጐን አስተያይ።
6. ከ8፥1-10 ከኢየሱስ አርአያነት ምን ትማራለህ?

8፥1 ብዙ ሕዝብ፤ እንርሱ በኩረል የተገኙት ከሰዎች አለመታዘዝ የተነሣ ነበር (7፥36)፤ ብዙዎቹ የእስራኤል ባሕል ካልተስፋፋበት፥ የአሥር ከተማ አገር ነዋሪዎች የነበሩ ይመስላል (7፥31)፤ ከዚህ አንጻር የተመገቡት 5000 ሰዎች በተለይ አይሁድ ነበሩ።

ሳምንት 10 እሑድ — ማርቆስ 8፥11-26

1. ፈሪሳውያን ምልክትን ከሰማይ በመፈለጋቸው ስለ ሁኔታቸው ምን ገለጡ (ቍ.11-12)?
2. የሃይማኖትና የፖለቲካ ሰዎች «እርሾ» የክርስቶስን መልእክት እንዴት ሊያደናቅፍ ይችል ነበር (15)? ዛሬ «የፈሪሳውያንና የሄሮድስ እርሻ» የት ይታያል?
3. ሐዋርያት የኢየሱስን ቃል ለምን አላስተዋሉም (16-21)?
4. «ሰዎች እንደ ዛፎች ሲመላለሱ አያለሁ» የሚለው ሐረግ በዚያን ጊዜ የነበረውን የሐዋርያትን ግስተዋል እንዴት ይገልጣል (24)?
5. ዛሬ ሰዎች ስለ ኢየሱስ፥ ሀ)የሚያስተውሉት፥ ለ)የማያስተውሉት ምንድን ነው?

ቍ.11 ከሰማይ ምልክት፤ እርሱ ራሱ ምልክቱ ቢሆንም፥ ፈሪሳውያን ግን ተልእኮውን የሚያረጋግጥ እንደ ሙና ወይም እንደ እሳት ያለ ነገር ይፈልጉ ነበር፤ ዮሐ.6፥30-32፤ 1ነገ.18፥36-38።

ቍ.15 ሄሮድስ፤ እንደ ፈሪሳውያን ምልክትን በመፈለጉ አለማመኑን ገለጠ፤ ሉቃ.23፥8።

ቍ.25...ደግሞ እጁን በዓይኑ ጫነበት፤ በዚህ ተአምር ብቻ ኢየሱስ ይህን ሰው በሁለት ደረጃዎች ፈወሰ፤ ሰውየው ማየት ቢጀምርም አጥርቶ ማየት ያስፈልገው ነበር።

ከዚህ ቀደም እንደተገለጸው ይህኛው ተአምርም ለምእመናን የሚሰጠው ትምህርት አለው።

ሳምንት 10 ሰኞ — ማርቆስ 8፥27-38

መግቢያ፤ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ስለ እርሱ ማንነትና ስለ ሥራው በይበልጥ ለማስተማር ከአስራኤል አገር ወደ ሰሜን ወሰዳቸው።

1. በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ ስለ ኢየሱስ ምን፥ ሀ) ተረድቶ ነበር (ቊ.27-30)፥ ለ) አልተረዳም (31-32)? ሐ) ለምን አጥርቶ አያይም ነበር (33)?
2. እውነተኛ ክርስቲያን፥ ሀ)ክርስቶስን፥ ለ)ራሱን፥ ሐ)ዓለምን እንዴት ይመለከታል ?
3. ክርስቶስን፥ ሀ)የመከተል፥ ለ)ያለመከተል፥ ዋጋ ምንድን ነው (34-38)?

ቊ.34 መስቀሉን ተሸክሞ ...፤ ይህም የዓለምን ተታውሮና መከራ በክርስቶስ ስም መቀበል ማለት ነው (38)።

መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ

እስራኤላውያን በኢያሱ መሪነት ወደ ከነዓን አገር ከገቡ በኋላ፥ እግዚአብሔር በመሳፍንት አማካይነት 300 ዓመት ያህል ሕዝቡን አስተዳደረ። ሳሙኤል ከመሳፍንቱ የመጨረሻው ሲሆን «ነቢዩ ሳሙኤል» በሚለው ስም የታወቀ ሆነ። ሐ.ሥ.3፥24፤ 13፥20። እርሱ ነቢያትን በቡድን አደረጋቸው፤ የእስራኤልን የመጀመሪያ ሁለት ነገሥታት ከብዙ ምክርና ማስጠንቀቂያ ጋር በመቀባት ንጉሣዊ አገዛዝን ለእግዚአብሔር ሕዝብ መሠረተ።

ሳምንት 10 ማክሰኞ — 1ሳሙኤል 1፥1-18

1. የሐና፥ ሀ)ሁኔታ፥ ለ)መንፈስ፥ እንዴት ነበር (ቊ.1-6)?
2. ሀ)ሕልቃና፥ ለ)ፍናና (ፈኒና) ሐናን እንዴት ይመለከቷት ነበር (4-8)?
3. ሐና በመጨረሻ ምን አደረገች? ምንስ ሆነ (9-17)?
4. አንተ በሕይወትህ ገና ትልቅ ጉድለት እንዳለብህ ይሰማሃልን? ከሆነ በምን አኳኋን ትጸልያለህ?
5. የዔሊ ቡራኬ በሐና ላይ ምን ለውጥ አመጣ (17-18)?
6. ይህ ምንባብ እግዚአብሔር በደካማ ሰዎች አማካይነት ዕቅዱን መፈጸም እንደሚችል እንዴት ያሳያል?

ቊ.2 ሁለት ሚስቶች፤ በሕግ ቢፈቀድም እንኳ (ዘዳ.21፥15-17)፥ የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ዕቅድ አልነበረም (ማቴ.19፥8)፤ ሁለቱ ባሎቿ ትዳር ደስታ አይገኝም ነበር።

ቊ.3 ሴሎ፤ ከኢየሩሳሌም በሰተ ሰሜን 30 ኪ.ሜ የሚርቅ ስፍራ። መሳ.20፥27ና ማስታወሻውን ተመ.።

ቊ.11 ምላጭም በራሱ ላይ አይደርስም፤ መሳ.13፥5፤ ዘኍ.6፥1-21 ተመ.።

ሳምንት 10 ረቡዕ — 1ሳሙኤል 1፥19-28፤ 2፥1-11

1. ሕልቃና ለሐና የነበረውን ፍቅር እንዴት አሳያት (1፥19-25)?
2. እንደ ሐና የጸሎትህን መልስ ብታገኝ ምን ታደርጋለህ (1፥26-27፤2፥1)?
3. ቃልህን ሁሉ እንደ ሐና ትፈጽማለህን (1፥28)?
4. የሐና ጸሎት የእግዚአብሔርን ሥልጣን እንዴት ያብራራል (2፥1-10)?
5. * የሐና መንፈሳዊ እድገት እንዴት ሆነ? ትልቁ ለውጥ የታየው መቼ ነበር (1፥8፡10-11፡ 18፡22፡26-27፤2፥1)?

ቍ.20 ሳሙኤል፤ የእግዚአብሔር ስም ወይም እግዚአብሔር ሰማ ማለት ይሆናል።

ቍ.21 ስእለቱን...፤ ሕልቃና የሚሰቱ ስእለት እንዲፈጸም ጎላፊነት የተሰማው ይመስላል፤ ዘኍ.30፥13-14።

ሳምንት 10 ሐሙስ — 1ሳሙኤል 2፥12-36

1. የዔሊ ልጆች እግዚአብሔርን እንዴት ናቁ (ቍ.12-17፡22)?
2. ሳሙኤል በዚህ አቅራቢያ ሲያድግ የወላጆቹን ትካዜ ገምት።
3. እግዚአብሔር የሐናን ጸሎትና አገልግሎት እንዴት ባረከ (18-21)?
4. የቤተሰብህን ተጽእኖ እንዴት ትመለከተዋለህ?
5. የዔሊ ምክር ለምን ከንቱ ሆነ (25-26፡29፤3፥13)?
6. በቍ.35 መሠረት ታማኝነትህን መርምር።

ቍ.16 ስቡን ያቃጥሉት፤ ስቡ የእግዚአብሔር ድርሻ ነበረ፤ ዘሌ.3፥3-5።

ቍ.22...ከሚያገለግሉት ሴቶች ጋር፤ ዘጸ.38፥8።

ሳምንት 10 ዓርብ — 1ሳሙኤል 3

መግቢያ፤ በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር በሕልም፥ በራእይ፥ በቃል፥ በተአምር፥ በሌላም ራሱንና ፈቃዱን ይገልጥ ነበር። ሕዝቡ ከመንገዱ ሲወጣ ግን እግዚአብሔር ከነርሱ ርቆ ብዙ አልተናገራቸውም።

1. ሳሙኤል ድምጹ የእግዚአብሔር መሆኑን ሊረዳ እንዴት በቃ (ቍ.1-9)?
2. ሳሙኤል ገና ልጅ ቢሆንም የእግዚአብሔርን ድምጽ ለመስማት ዝግጁ ስለመሆኑ ከጠባዩ ምን ይታያል (1-10)?
3. እግዚአብሔርን አውቃለሁ ማለት ትችላለህን? ድምጹን መቼ ሰማህ? እግዚአብሔር እንደሚናገርህ በምን ታውቃለህ?
4. ሳሙኤል መልእክቱን ከተቀበለ በኋላ፥ ሀ)ወዲያው፥ ለ)ዔሊ ሲጠይቀው፥ ሐ)በሚቀጥሉት ዓመታት ምን አደረገ (15-21)?

ቍ.1 ብላቴናው (ወጣቱ)፤ ቃሉ እድሜው 12 ዓመት ያህል መሆኑን ያመለክታል።

ቍ.9 ቢጠራህም ...፤ ሰው የእግዚአብሔርን ድምጽ ለመስማት ሲፈልግ፥ ዋናው ነገር የራሱ ዝግጁነት እንጂ የእግዚአብሔር አስተዋይነት ወይም ደግነት አይደለም።

ቍ.20 ዳን...ቤርሳቤህ፤ በሰሜንና በደቡብ እስራኤል የሚገኙ የመጨረሻ ከተሞች።

ሳምንት 10 ቅዳሜ — 1ሳሙኤል 4

1. ለሽማግሌዎቹ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ምን ነበር (ቍ.3)?
2. ሀ) እስራኤል (3-5)፥ ለ) ፍልስጥኤማውያን፥ የተሳሳቱበት ነገር ምን ነበር (6-9)?
3. ሰዎች ዛሬ ይህን የመሰለውን ስሕተት እንዴት ይፈጽማሉ?
4. ዔሊና የፊንሐስ ሚስት የሽንፈቱን ወሬ እንዴት ተቀበሉ (12-22)? ለምን?
5. የእግዚአብሔር ሥራ መዋረዱን ብትሰማ ምን ይሰማሃል? ለምን?
6. የዔሊን ደግነት ከአኗኗቱ ጋር አስተያይ።

ቍ.2 ፍልስጥኤማውያን በእስራኤል ላይ ተሰለፉ፤ አውን እስራኤልን ለመግዛት የፈለጉ ይመስላል። መሳ.13፥1ና ግስታወሻውን ተመ.።

ቍ.4 ታቦት...፤ ዘጸ.25፥10-22። ታቦቱ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር መኖሩን የሚያሳይ ምልክት ነበር፤ ሕዝቡ ሕጉን ሲተላለፍ ግን ተሰሚነት አልነበራቸውም፤ መዝ.65(66)፥18።

ሳምንት 11 እሑድ — መዝሙር 58(59)

መግቢያ፤ ሳኦል ዳዊትን ግሳደድ ሲጀምር፥ ቤቱን ከበው በግለጻ እንዲገድሉት ሰዎችን ላከ። በሚስቱ በሜልኮል (በሚካል) አማካይነት ዳዊት እንዴት እንዳመለጠ በ1ሳሙ.19፥1-18 ተጽፎ ይገኛል። ይህም መዝሙር በዚያን ጊዜ ለእግዚአብሔር ያቀረበው ጸሎት ነው።

1. ዳዊት ስለ ጠላቶቹ ምን ገለጠ (ቍ.1-3፡7)?
2. ሀ) በቍ.4 እና 5 በሚገኙት ልመናዎች መካከል ምን ግንኙነት አለ? ለ)አንተ ልመናህን በግል ጀምረህ ለሌሎች ጸሎትህን እንዴት ታስፋፋለህ?
3. ዳዊት እግዚአብሔርን ስለ ምን አመሰገነ (5፡9-10፡16-17)?
4. የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች ፍርድ ለጊዜው ለምን መጠነኛ ሆነ (11-13፤ 57(58)፥11)?
5. እግዚአብሔር መጠጊያህ በመሆኑ በዛሬው ሕይወትህ ላይ ምን ለውጥ ያመጣል?

ቍ.8 መዝ.2፥4 ተመ.።

ቍ.11 ሕግህን እንዳይረሱ፤ ባለቤቱ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው።

አትግደላቸው፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶችን ያመለክታል።

ሳምንት 11 ሰኞ — 1ሳሙኤል 5፥1-12፤ 6፥1-12

መግቢያ፤ ታቦቱ በፍልስጥኤማውያን ሲማረክ እስራኤል በሐዘን ተሞላ። መዝ.77(78)፥56-64፤ ኤር.7፥12፤26፥9። እግዚአብሔር ግን ስሙን በመቅሠፍት አስከበረ።

1. ፍልስጥኤማውያን ታቦቱን ሲይዙ ሐሳባቸው ምን ነበር (5፥1-2)?

2. እግዚአብሔር ግን የበላይነቱን እንዴት አሳየ (5፥3-5)?

3. ታቦቱን ወደ እስራኤል አገር እንዲልኩት እግዚአብሔር ምን አደረገ (5፥6-12)?

4. ፍልስጥኤማውያን ታቦቱን በምን አኳኋን ላኩት (6፥1-12)? ለምን (6፥3፡9)?

5. ዛሬ እግዚአብሔር ክብሩን እንዴት ይጠብቃል?

6. እግዚአብሔር በላከውና በሌሎች ነገር መካከል ያለውን ልዩነት ለማወቅ ትኖርሪለህን? ለምን? ልዩነቱን ለማወቅ የምትኖርክ ከሆነ እንዴት?

5፥1 አሽዶድ፤ የሚ.13፥17 ማሕታወሻ ተመ.።

5፥2 ዳጎን፤ ከፍልስጥኤማውያን አማልክት ዋናው ነበር። ታቦቱን በዳጎን አጠገብ በማኖራቸው የአምላካቸውን የበላይነት ለማሳየት የሞከሩ ይመስላል።

5፥3 በግምባሩ መድቶ ነበር፤ እንደ ባርያ በጌታው ፊት።

ሳምንት 11 ማክሰኞ — 1ሳሙኤል 6፥13-21፤ 7፥1-14

1. ሀ) የቤትሳሚስ ሰዎች እግዚአብሔርን በምን አኳኋን አመለኩ (6፥13-18)? ለ) እግዚአብሔር ለምን ቀሠፋቸው (6፥19-21)?

2. ከዚህ በኋላ ታቦቱ የት ተቀመጠ (7፥1-2)?

3. ሳሙኤል ከሃያ ዓመት አገልግሎት በኋላ (7፥2፤3፥21) እስራኤልን ወደ ንስሐ እንዴት መራቸው (7፥3-6)?

4. እስራኤል ከሃያ ዓመት በፊት በተሸነፈበት ስፍራ እንዴት ድል ነሣ (7፥7-11)?

5.* ከሳሙኤል ስለ ጸሎት፥ ሀ)ጊዜ፥ ለ)መንፈስ፥ ሐ)ኃይል፥ መ)መታሰቢያ ምን ትማራለህ (7፥2፡8-14)?

6. አንድ ሕዝብ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ከወጣ በኋላ በረከቱን እንደገና እንዴት ሊያገኝ ይችላል?

6፥19 ሰባ ሰዎችን መታ፤ እግዚአብሔር በፍልስጥኤማውያን ላይ ክብሩን እንደጠበቀ ሁሉ፥ በሕዝቡም ዘንድ ቅድስናውን ጠበቀ፤ ዘኁ.1፥50-51፤ 4፥5፡16-20።

7፥6 ውኃ...አፈሰሱ፤ የስርየት ሥርዓት ይመስላል፤ ሰ.ኤ.2፥19 ተመ.።

7፥12 አቤንኤዘር፤ የእርዳታ ዓለት ማለት ነው፤ 4፥1-4።

ሳምንት 11 ረቡዕ — 1ሳሙኤል 7፥15-17፤ 8፥1-22

መግቢያ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ሳሙኤል ብዙ ዓመት የደከመበትን አገልግሎት በአጭሩ ያቀርባል። በኋላ ግን ሳሙኤል ከባድ ጥያቄ ተጠየቀ፤ ይህም ለእስራኤል አገዛዝ ከፍ ያለውን ለውጥ አመጣ።

1. ሳሙኤል እስራኤልን እንዴት አገለገለ (7፥15-17)?

2. የሳሙኤል ልጆች በመንገዱ ያልሔዱበት ምክንያት ምን ይመስልሃል (8፥1-5)?

3. የሽማግሌዎች ልመና ሳሙኤልን ለምን አስከፋው (8፥4-8)?

4. ሰዎች ሲያስከፉህ ምን ታደርጋለህ? ትቈጣለህን? ታማለህን? ስም ታጠፋለህን? ቸል ትላለህ? ትጸልያለህን? በአዲስ ሁኔታ የተሻለውን መንገድ ትፈልጋለህን?

5. ሕዝቡ «እንደ አሕዛብ ሁሉ እንሆናለን» በማለታቸው ምን አሳዩ (8፥7፡ 19-22)?

6. እግዚአብሔርን የማያውቁትንና የማያከብሩትን ሰዎች አካሄድ ምን ያህል ትከተላለህ?

<u>8፥2 በቤርሳቤህ</u>፤ ሳሙኤል ከኖረበት የሚርቅ የመጨረሻ የእስራኤል ከተማ።

<u>ሳምንት 11 ሐሙስ</u> <u>1ሳሙኤል 9፥1-25</u>

1. ከዚህ ምንባብ ስለ ሳኦል ቤተሰብ፥ መልክ፥ ሥራና ጠባይ ምን ትማራለህ (ቊ.1-7፡19-21)?

2. ሳኦል ከሳሙኤል ጋር እንዲገናኝ ምን አጋጣሚ ነገር ነበር (3-14)?

3. ሳሙኤል ሳኦልን እንዴት አወቀ (15-16)? ምን አደረገለት (17-25)?

4. ሳኦል የእስራኤል ንጉሥ ስለ መሆን ያልተረዳው ነገር ምን ነበር (21፤15፥17)?

5. እግዚአብሔር የሚሆንልህን ሁሉ አስቀድሞ እንደወሰነ ታምናለህን (ሮም 8፥28-30)? እያንዳንዱ ነገር በሕይወትህ ምን ግብ እንዳለውም፥ ሀ)ሲሆን፥ ለ)ከሆነ በኋላ ለማስተዋል ትችላለህን? ለእያንዳንዱ ነገር ግብ መፈለግ ይገባሃልን? ለምን?

<u>ቊ.6</u> ብላቴናው እንጂ ሳኦል ወደ ሳሙኤል መሔድ አላሰበም።

<u>ሳምንት 11 ዓርብ</u> <u>1ሳሙኤል 9፥26-27፤ 10፥1-27</u>

<u>መግቢያ</u>፤ በዚህ ምንባብ ሳኦል መጀመሪያ ንጉሥ እንዲሆን በግል ሲቀባ፥ በኋላም በሕዝብ ፊት ሲመረጥና ሲለይ ይታያል።

1. ሳሙኤል ሳኦልን ሲቀባ ምን ሦስት ነገር አደረገለት (10፥1)?

2. ሀ) እግዚአብሔር የሳኦልን መመረጥ በምን ሦስት ምልክት አረጋገጠለት (10፥2-8)? ለ)ለንጉሥ ሥራ እንዲበቃ ምን ተደረገለት (10፥9-13)?

3.* የእግዚአብሔር ፍቅርና ትእግሥት ለሕዝቡ በምን ይታያል (10፥1፡18-19)?

4. ሳሙኤል ሳኦልን በሕዝብ ፊት እንዴት አከበረው (10፥20-25)?

5. ሳኦል ጥበብን እንዴት አሳየ (10፥11፡16፡27)?

6. ከርስቲያን ግናቸውንም ዓይነት አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት፥ የእግዚአብሔር ጥሪ፥ የግል ዝግጅትና በምእመናን መታወቅ እንዴት ሊገናኙ ይችላሉ?

10፥5 የነቢያት ጉባኤ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ የነቢያት ቡድን ተጠቅሶአል።

10፥9 ሌላ ልብ ለወጠለት፤ ከገበሬ ልጅነት ወደ ጦር መሪነትና ሕዝብ አስተዳዳሪነት።

10፥11 በእውኑ ሳኦል ከነቢያት ወገን ነውን?፤ ጓደኞቹ የሃይማኖት ልምድ የሌለው፥ ትንቢትን ሲናገር በማየታቸው ተገረሙ፤ 9፥6ና ማስታወሻ፤ 19፥24።

10፥12 አባታቸውስ ማን ነው? (የእነዚህስ የሌሎቹ ነቢያት ሁኔታ እንዴት ነው? አባቶቻቸውስ እንማን ናቸው?)፤ ልብን የሚለውጥ እግዚአብሔርን ወይም በነቀፌታ ሳሙኤልን ሊያመለክት ይችላል።

10፥25 በእግዚአብሔር ፊት አኖረው፤ በታቦቱ ፊት።

ሳምንት 11 ቅዳሜ — 1ሳሙኤል 11

1. የኢያቢስ ሰዎችና ሌሎች አለማመናቸውን እንዴት ገለጡ (ቊ.1-4)?
2. አንተ ስትቸገር ወደ ማን ትሔዳለህ? ለምን?
3. የኢያቢስን ሰዎች ለማዳን፥ ሀ)ሳኦልን፥ ለ)እስራኤልን የገፋፋው ምን ነበር (6-7)?
4. ስለ ጭቄና ስትሰማ ምን ይሰማሃል? ምንስ ታደርጋለህ? ለምን?
5. ሳኦል የመሪነትን ችሎታ እንዴት አሳየ (7-13)?
6. ሳሙኤል ንጉሣዊ አገዛዝን ለማጽናት ምን አደረገ (14-15)?

ቊ.1 ኢያቢስ ገለዓድ፤ የሃይማኖት ድክመት የነበረበት ቦታ፤ መሳ.21።

ቊ.7 ጥምዱንም በራዎች ወስዶ ቈራረጣቸው፤ መሳ.19፥29 ተመ.።

ቊ.15 ሳኦልን...አነገሡት፤ ሳኦል በሳሙኤል ተቀባ (10፥1)፥ በሕዝብ ፊት ታወጀ (10፥25-27)፥ በመጨረሻም በሁሉ ፊት እንደ ንጉሥ ታወቀ።

ሳምንት 12 እሑድ — መዝሙር 59(60)

መግቢያ፤ ዳዊት ሞዓባውያንንና ሶርያውያንን ሲያሸንፍ ሳለ (2ሳሙ.8፤1ዜ.መ.18 ተመ.)፤ ኤዶም በደቡብ ይሁዳ አደጋ የጣለ ይመስላል።

1. ድል ሲነሡና በሌላ አቅጣጫ ድንገት ሲሸነፉ ዳዊትና ሕዝቡ ምን ተሰማቸው (ቊ.1-3)?
2. በሕይወትህ እንደዚህ ያለ ነገር ደርሶብህ ያውቃልን? እግዚአብሔር ምን ያስተማረህ ይመስልሃል?
3. በቊ.6-8 ዳዊት እግዚአብሔርን በምን አኳኋን ይገልጠዋል?
4. በቊ.9-12 የዳዊትን ልዩ ልዩ የእምነት ደረጃዎች ዘርዝር።
5. የዳዊትንና የሕዝቡን እምነት ለማጽናት እግዚአብሔር የሰጠው «ምልክት» ምን ይመስልሃል (4፥6-8)?

6. ሰይጣን በእንተ ላይ አደጋ በጣለ ጊዜ፥ እግዚአብሔር ምን "ምልክት" ሰጠህ?

ኢዮአብ፤ የዳዊት ሠራዊት አለቃ።

ቍ.6 በትድስናው (በመትደሰ)።

ሳምንት 12 ሰኞ — 1ሳሙኤል 12

መግቢያ፤ ሕዝቡ ሁሉ ሳኦልን እንደ ንጉሣቸው ሲቀበሉት፥ ሳሙኤል የአስተዳደሩን ሥራ መተው በመቻሉ አደራውን በሳኦልና በሕዝቡ ላይ ጣለ።

1 ሳሙኤል ሕዝቡን ሲያሰናብት፥ ሀ)አገልግሎቱን ለምን አጸደቀ (ቍ.1-4)፥ ለ)የእስራኤልን ታሪክ ሲተርክ በምን ላይ አተኰረ? ለምን (5-19)? ሐ)የበረከትን መንገድ እንዴት ገለጸ (20-25)?

2.* የአስተዳደር መንገድ ሲለወጥ በመሠረቱ ምን ለውጥ ተገኘ? ከዚህ ምን ትማራለህ?

3. ከዚህ ምንባብ ስለ ሳሙኤል ዓላማ፥ ታማኝነት፥ እምነትና ጸሎት ምን ታስተውላለህ?

4. ሳታቋርጥ ለማን ትጸልያለህ? ለምን?

ቍ.12 ናዖስ፤ ንጉሥ እንዲኖራቸው የእስራኤልን ፍላጎት ያጸና የአሞን ኃይል ዕድገት የነበረ ይመስላል።

ቍ.23 ንጉሥን መፈለጋቸው ሳያስቀይመው፥ የአስተዳደርን ሥራ ትቶ የነቢይንና የካህንን ሥራ በሙሉ ልብ መከተሉ የሳሙኤልን ታላቅነት ያሳያል።

ሳምንት 12 ማክሰኞ — 1ሳሙኤል 13

1. በእስራኤልና በፍልስጥኤማውያን መካከል ምን ሆነ (ቍ.1-7)?

2. የሳኦልን ስሕተት ዘርዝር፤ ምን ምክንያት አቀረበ? ይህም ስለ ልቡና ስለ እግዚአብሔር የነበረውን አስተሳሰብ ምን ያሳያል (8-14)?

3. እግዚአብሔርን ለማስገደድ ሞክረህ ታውቃለህን? ምን ሆነ?

4. የእስራኤል ተስፋ በጦርነት እንዴት ነበር (15-23)?

5. የእግዚአብሔርን ጊዜ ለመጠበቅና እምነትህን ለማጠንከር እንዴት ትችላለህ?

ቍ.4 ጌልገላ፤ የ10፥8 ትእዛዝ የተደገመ ይመስላል።

ቍ.5 ማክማስ፤ በቤቴልና በጌልገላ መካከል ባለው ተራራማ አገር የመተላለፊያ ስፍራና ትንሽ ከተማ።

ሳምንት 12 ረቡዕ — 1ሳሙኤል 14

መግቢያ፤ ሳኦል ከእግዚአብሔር ፈቃድ ወጥቶ ነበር፥ እግዚአብሔር ግን ሕዝቡን ለማዳን በሌላ መንገድ ዕቅዱን ፈጸመ።

1. የዮናታንን ድፍረትና ውጤቱን መርምር (ቍ.6-14)።

2. አጉል ድፍረትንና እውነተኛ ድፍረትን እንዴት ትለያለህ?

3. ሳኦል በመቸኩሉ (19) ምን ስሕተት ሠራ (24፡29-30)?

4.* ሳኦል እግዚአብሔርን ለማሳዘን እንዳልፈለገ ምን ማስረጃ አለ (18፡24፡32-39፡45)?

5.* ሰው በአንድ በኩል በራሱ ፈቃድ ሲመራ፥ በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔርን ለማሳዘን ባይፈልግ ውጤቱ ምን ይሆናል?

6. ሳኦል ለእስራኤል ምን አደረገ (47-48)?

ቍ.3 ኤቶድም የለበሰ፤ ቍ.18፡36-42 ተመ.።

ቍ.6 እንለፍ፤ 5 ኪ.ሜ. ያህል ነው።

ቍ.24 ሳኦል...አምሉአቸው ነበር፤ ሳኦል በጾም የእግዚአብሔርን በረከት ለማስገኘት ያሰበ ይመስላል፤ ዮናታን ግን የታወጀውን ጾም ሳያውቅ ቀርቶ መሃላውን አልጠበቀም።

ቍ.32 ...ከደሙ ጋር በሉ፤ ዘሌ.17፥10-14፤22፥28።

ሳምንት 12 ሐሙስ — 1ሳሙኤል 15

መግቢያ፤ ሳኦል ለእግዚአብሔር እንዲታዘዝ ሌላ ዕድል ተሰጠው። በፊተኛው ጊዜ በፍልስጥኤማውያን መምጣት ብዙ ግፊት ነበረበት (13፥11-12)፥ አሁን ግን ፈተናው የደረሰበት ድል ከኾነ በኋላ ነበር።

1. ሳኦል የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ምን ያህል ፈጸመ (ቍ.7-9)?

2. ሳኦል፥ ሀ) እግዚአብሔርን፥ ለ) ሳሙኤልን እንደናቀ በምን ይታያል (12፡13፡15፡20-21)?

3. ሰው የሃይማኖትን ሥርዓት በመፈጸም አለመታዘዙን መሸፈን ይችላልን? ለምን(15፡21-23፡30-31)?

4. የሳኦል ዋና ኃጢአትና ውጤቱ ምን ነበር (23፡26)?

5. በአንዳንድ ነገር ለእግዚአብሔር ላለመታዘዝህ ምን ምክንያት ታቀርባለህ ወይም ክፋትህን ለመሸፈን እንዴት ትሞክራለህ?

6. ሳሙኤል በሳኦል አለመታዘዝ ምክንያት ምን አደረገ (10-11፡32-35)?

ቍ.2 አግሌት፤ ዘጸ.17፥8-16፤ዘዳ.25፥17-19።


ቍ.12 የመታሰቢያ ዓምድ (ለራሱ ሐውልት)፤ በራት ድል ሲነሣ እግዚአብሔርን አክብሮ ነበር፤ 11፥13፤14፥35።

ቍ.21 ለአምላክህ፤ ሳኦል አምላኮችን አላለም (15)፤ ቢሆንም የሃይማኖትን ስፍራ በእስራኤል አወቀ (24-31)።

ሳምንት 12 ዓርብ — 1ሳሙኤል 16

መግቢያ፤ ሳሙኤል በእግዚአብሔር ትእዛዝ ሳኦልን ከቀባ በኋላ «ከሕዝቡ ሁሉ እርሱን የሚመስል እንደሌለ እግዚአብሔር የመረጠውን ታያላችሁን?» ብሎ ለእስራኤል አቀረበው። 10፥24። ሳሙኤል በሳኦል ተስፋ አድርጎ ሳለ፥ ሳኦል ግን ከእግዚአብሔር መንገድ በመውጣቱ ሊሻር ነበር። የሚተካው «ለእግዚአብሔር እንደ ልቡ የሆነ ሰው (13፥14)» ከዓለምም ታላላቆች ሁሉ አንዱ ነው።

1. ሳሙኤል በምን መንፈስ ለእግዚአብሔር ታዘዘ (ቊ. 1-6)?
2. ሳሙኤል አሁን ምን ተግረ (7-12)?
3. አንተ በምን መሠረት ሰዎችን ትመዝናቸዋለህ? ለምን?
4. ዳዊት እንዴት ያለ ነበር (11-12)?
5. እግዚአብሔር ለሥርዓተ ንግሥና ዳዊትን እንዴት አዘጋጀው (13-23)?
6. እግዚአብሔር ለአገልግሎት ሲያዘጋጅህ ምን ተምረሃል?



ቊ.1 እሴይ፤ ሩት 4፥13-22 ተመ.።

ቊ.7 የቱሙትንም ዘለግታ፤ ከ9፥2 ጋር አነጻጽር።

ቊ.11 ታናሹ ገና ቀርቶአል ...፤ ዳዊት የእሴይ ልጅ ሲሆን፥ እናቱ የሰባቱ ወንድሞች እናት የነበረች አይመስልም።

ቊ.14 የእግዚአብሔርም መንፈስ ከሳኦል ራቀ ...፤ ከቊ. 13፤ 10፥9-10 እና 11፥6 ጋር አነጻጽር፤ ደግሞም የመሳ. 15፥14ን ማስታወሻ ተመ.።

ቊ.21 ጋሻ ጃግሬው ሆነ፤ ጎልያድን ከገደለ በኋላ ይመስላል። 18፥2።

ቊ.23 ከቶ መንፈስ፤ አልፎ አልፎ መጣበት፤ 18፥10።

ሳምንት 12 ቅዳሜ — 1ሳሙኤል 17

መግቢያ፤ ዳዊት በሳሙኤል ተቀብቶ ነበር፥ ነገር ግን እስራኤል ሁሉ እንደ ንጉሣቸው እስኪቀበሉት ድረስ ሃያ ዓመት ገና አልሞላውም ነበር።

1.* ሳኦል፥ ዮናታንና እስራኤላውያን ሁሉ ፍልስጥኤማዊውን ከመጠን በላይ ለምን ፈሩ (4፥10፤ 16፥14 ተመ.)?
2. ስለ ዳዊት ሁኔታ በቤተሰቡ ከኤልያብ ጋር ካደረገው ንግግር ምን ታስተውላለህ (ቊ. 28-30)?
3. ዳዊት ጎልያድን ለመግጠም እንዴት በታ (34-40፡45-47)?

4. አሁን በሕይወትህ ዋናው ትግል ምንድን ነው? ይህ ትግል፥ ሀ) ለዕድገትህ፥ ለ) በሕይወትህ ላጋጠሙህ ዋና ነገሮች፥ ሐ) ለእምነትህ፥ መ) ለዋና የሕይወትህ ዓላማ፥ እንዴት አዘጋጀህ?

ቍ.15...ይመላለስ ነበር፤ 16፥19-23ና ማስታወሻን ተመ.።

ቍ.28 የኤልያብም ቍጣ፤ የዳዊትን መቀባት የነቀፈ ይመስላል፤ 16፥7-13።

ሳምንት 13 እሑድ — መዝሙር 60(61)

መግቢያ፤ በዚህ መዝሙር በድሮውና በአዲሱ ትርጒም መካከል የሚታየው ልዩነት የመጣው፥ ሁለቱም ከተለያዩ የእጅ ጽሑፎች በመተርጐማቸው ይመስላል። ቀጥለው ያሉት ጥያቄዎች በድሮው ትርጒም ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

1. ዳዊት እግዚአብሔር ሩቅ መሆኑ ሲሰማው ምን አደረገ (1-2)?
2. እግዚአብሔር ለዳዊት ምን እንዳደረገለትና ለወደፊት ምን እንደሚያደርግለት ዘርዝር።
3. እግዚአብሔር ለልመናው መልስ ስለ ሰጠ በዳዊት ሕይወት ምን መልካም መንፈሳዊ ፍሬ ይታያል(4፡8)?
4. ተስፋ የሚያስቆርጥ ሁኔታ ደርሶብህ ያውቃልን? ምን አደረግህ? በሕይወትህ ምን መንፈሳዊ ፍሬ ታየ?

ቍ.8 ስእለቴን (ለአንተ የተሳልሁትን)፤ አብዛኛው ጊዜ ስእለት በአንድ ሥርዓት ይፈጸም ነበር። ዘሌ.7፥16። ዳዊት ግን ዘወትር እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባው ተሰማው።

ሳምንት 13 ሰኞ — 1ሳሙኤል 18

1. ከጦርነቱ በኋላ፥ ሀ)ሳኦል፥ ለ)ዮናታን ለዳዊት ምን አደረጉ (ቍ.1-5)?
2. በታላቅ ወንድሙ ለተነቀፈው ወጣት (17፥28) ተቀባይነት ማግኘቱ ምን ያደርግ ነበር?
3. ሳኦል በዳዊት ላይ ቅንዓትና ፍርሃት ለምን አደረበት (6-9፡12፡15፡28-29)?
4. ሳኦል ዳዊትን ለመግደል እንዴት ሞከረ (11፡17፡21፡24-25)?
5. የቅንዓት መንፈስ በአንተ ላይ ይነሣልን? ለምን? እንዴት ታስወግደዋለህ?
6. ዳዊት የሳኦልን ጥላቻ እንዴት ታገሠ (14-16፡18፡23፡26፡30)? የሰውን ተቃውሞ ትታገሣለህን? እንዴት?

ቍ.10 ክፉ መንፈስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያዘው ...፤ ይህ ለኃጢአቱ ቅጣት ነበር፤ ቍ.9፤ 16፥14፤ 1ነገ.22፥20-22።

ሳምንት 13 ማክሰኞ — 1ሳሙኤል 19

1. ዳዊት እንዳይገደል ዮናታን ለሳኦል ምን ምክንያት አቀረበ (ቍ.1-7)?
2. ክፉ መንፈስ በሳኦል ላይ እንደገና ለምን ተነሣ (8-10)?

3. አንተ የምትመራው በጊዜአዊ ሰሜትህ ነው ወይስ ትክክለኝነት ባላቸው መሠረታዊ ሐቆች?

4. ሚካል ዳዊትን በምን አኳኋን ረዳው (11-17)?

5. እግዚአብሔር ዳዊትን አሁን ከሳኦል ጥላቻ እንዴት አዳነው (18-24)?

ቍ.13 ተራፊም (ቤተሰብ የሚያመልከው ጣዖት)፤ ሳሙኤል ስለ ባዕድ አምልኮ እስራኤልን አስጠንቅቆ ነበር፤ 7፥3፤ 15፥23።

ቍ.24 ሳኦል ደግሞ ከነቢያት መካከል ነውን?፤ ተረቱ ጸና፤ የ10፥11 ማስታወሻን ተመ.።

ሳምንት 13 ረቡዕ — 1ሳሙኤል 20

1. ዮናታን ፍቅሩን ለዳዊት እንዴት ገለጠ (ቍ.1-17)?

2. ስለ ዳዊት የሳኦልን ልብ ሐሳብ ለማወቅ ምን ዐቀዱ (18-23)?

3. ዮናታን ሁሉ ነገር ከእግዚአብሔር በታች መሆኑን እንዳመነ እንዴት አሳየ (22)?

4. እግዚአብሔር በሕይወትህ ከሚያጋጥምህ ሁሉ በላይ መሆኑን ማወቅህ እንዴት ይረዳሃል?

5. ዮናታንና ዳዊት የሳኦልን ልብ ሲያውቁ ምን አደረጉ (32-42)?

ቍ.2 ይህንስ ያርቀው፤ ዮናታን አባቱን በማክበር የአባቱ አጉል መንፈስ እንደሚያልፍ ተስፋ አደረገ፤ ዳዊት ግን የሳኦልን የልብ ዝንባሌ ተረድቶ ነበር (3)።

ቍ.41 በግምባሩ ተደፋ፤ ዳዊት ዮናታንን እንደ ንጉሥ ልጅ አከበረው።

ሳምንት 13 ሐሙስ — 1ሳሙኤል 21 እና 22

1. ዳዊት የፈለገውን ከአቢሜሌክ በምን አኳኋን አገኘ (21፥1-9)?

2. ዳዊት ከጌት ንጉሥ እንዴት አመለጠ (21፥10-22፥1)?

3. በዚህ ጊዜ ዳዊትን የገፋፋው ምን ነበር (21፥10፡12)?

4. ከሚያስፈራህ ሁኔታ ለመውጣት ሰውን ማታለል ይፈቀድልሃልን (ምሳ.29፥25)?

5.* ለኖብ ካህናት ምን ሆነ? ለምን (22፥6-19)?

6. ለዳዊት እንግን ደረሱለት? ለወላጆቹ ምን አደረገ (22፥1-5፡20-23)?

21፥1 ኖብ፤ ከኢየሩሳሌም ያልራቀ መንደር። ኢሳ.10፥32።

21፥6 ገጸ ኅብስት፤ ይህ በካህናት ይበላ ነበር፤ ዘሌ.24፥5-9፤ ማር.2፥23-26።

22፥3 የሞዓብንም ንጉሥ...፤ ሞዓባዊት ሩት የዳዊት ቅድመ አያት ነበረች፤ ሩት 4፥18-22።

22፥5 ጋድ፤ ለመጀመሪያ ጊዜ በዳዊት ታሪክ ይጠቀሳል።

22፥7 ብንያማውያን ሆይ...፤ ሳኦል በወገናዊነት አባበላቸው።

22፥20 አብያታር፤ እስከ ዳዊት ሞት ድረስ ሊቀ ካህናት ሆነ። በዚህ ጊዜ ወደ ዳዊት የመጡ ሰዎች በኋላ በመንግሥቱ የታወቁ ሆኑ።

ሳምንት 13 ዓርብ — 1ሳሙኤል 23

1. ዳዊት የቅዒላን ከተማ ለማዳን ምን አደረገ (ቍ.1-5)?
2. እንተ እንድን ነገር ከመወሰንህ በፊት ትጸልያለህን (2-4፡10-12)?
3. ከዮናታን ስለ እውነተኛ ወዳጅነት ምን ትማራለህ (16-18)?
4. እግዚአብሔር ዳዊትን እንዴት አዳነ (24-29)?

ቍ.5 ዳዊትና ሰዎቹ...ገደሉአቸው፡ በመጀመሪያው ዘመቻ ድል ነሡ፤ በኋላም እነዚህ ችግሮች (22፡2፤23፡13) የዳዊት ሠራዊት መሠረት ሆኑና እንድም ጊዜ አልተሸነፉም። በዓለም ታሪክ ከዳዊት የሚበልጥ መሪ አልተገኘም።

ሳምንት 13 ቅዳሜ — 1ሳሙኤል 24

1. ዳዊት ሳኦልን በቀላሉ ለመግደል እንዲችል ምን ሆነ (ቍ.1-3)?
2. ዳዊት ለምን አልገደለውም (4-7)?
3. ዳዊት ሳኦልን እንዴት አከበረ? አካሔዱን እንዴት አጸደቀ? ምን ተሰፋ ሰጠው (8-16፡20-22)?
4. ሰዎች መጥፎ ነገር ቢሠሩብህ ከዳዊት ሕይወት ምን ትምህርት ታገኛለህ (ሮም 12፡19-20)?
5. በወላጆችህ፡ በቤተ ክርስቲያንህ መሪዎች፡ በመንግሥት ባለሥልጣናት፡ በአሠሪዎችህ፡ በመምህሮችህ፡ በስፖርት ጎላፊዎችህ፡ ከእንተ በላይ ባሉት በሌሎችም ፊት፡ አካሔድህን ግጽደቅ ትችላለህን?
6.* ሳኦል ለምን አለቀሰ (16-22)?

ቍ.4 የሳኦልን መጐናጸፊያ ዘርፍ በቀስታ ቈረጠ፡ መንግሥቱን ከሳኦል የመረከብ ምሳሌ፤ ቍ.5፤15፡27-28።

ሳምንት 14 እሑድ — መዝሙር 61(62)

መግቢያ፡ አድመኞች ዳዊትን ከሥልጣን ለማውረድ ሲሞክሩ፡ ዳዊት በእግዚአብሔር አምኖ የልብ ዕረፍት እንዳገኘ በዚህ መዝሙር ይገልጣል።

1. በዳዊትና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ግንኙነት ግለጥ (ቍ.1-2)።
2. በቍ.3-4 ዳዊት፡ ሀ) ስለ ጠላቶቹ፡ ለ) ስለ ራሱ ምን ይገልጣል?
3. ዳዊት፡ ሀ) ለራሱ (5-7)፡ ለ) ለሕዝቡ (8-10) ምን ምክር ይሰጣል?
4. ከዚህ ሁሉ ሁኔታ ዳዊት ስለ እግዚአብሔር የተማራቸውን ሦስት ነገሮች ዘርዝር (11-12)?
5. ስትጨነቅ የልብህን ሰላም እንድትጠብቅ ይህ መዝሙር እንዴት ሊረዳህ ይችላል?

ኤዶታም፡ የመዝ.38(39) ግስታወሻን ተመ.።

ቍ.1 ነፍሴ ለእግዚአብሔር የምትገዛ አይደለችምን? (እግዚአብሔርን በትዕግሥት እጠባበቃለሁ)፤ ነፍሴ በእግዚአብሔር ብቻ ታርፋለች ወይም በእግዚአብሔር ፊት ዝም ትላለች፤ ቍ.5 ተመ.።

ቁ.12 የመጨረሻው የፍርድ ቀን ብቻ ሳይሆን፥ በሁሉ ነገር እግዚአብሔር በጽድቅ እንደሚፈርድ ማመልከቱም ነው።

ሳምንት 14 በኛ

1ሳሙኤል 25

1.* እስራኤል ሁሉ ለሳሙኤል ለምን አለቀሱ (1፥28፤2፥35፤ 12፥2-5)? ታላቅነቱ እንዴት ነበረ፤ መዝ.98(99)፥6፤ ኤር.15፥1፤ ሐ.ሥ.3፥24፤13፥20፤ ዕብ.11፥32?

2. ዳዊት በዚህ ጊዜ እንዴት ይኖር ነበር (ቁ.2-17)?

3. ቁ.21-22ን ከ24፥11-12 ጋር አነጻጽር፤ ልዩነቱን የፈጠረው ምን ነበር?

4. አቢግያ እንዴት ያለች ሴት ነበረች (14-31፥40-42)?

5. አንተ ለመበቀል ትሞክራለህ ወይስ ለእግዚአብሔር ፍርድን ትተዋለህ? 15፥12።

ቁ.2 ተርጌሱስ፤ ከኬብሮን በስተ ደቡብ 16 ኪ.ሜ. የሚርቅ ስፍራ።

ቁ.7 ዳዊት የራሱን መንን ይውሰን ይረዳ ነበር፤ 23፥1-5።

ቁ.43 ሚስቶች፤ 1ዜ.መ.3፥1-3 ተመ.።

ሳምንት 14 ሚከሰኛ

1ሳሙኤል 26 እና 27

1. ዳዊት የሳኦልን ሰፈር በምን አኳኋን ሰለለ (26፥1-12)?

2.* ሳኦል እንዳይገደል ዳዊት አሁን ምን ተጨማሪ ምክንያት አቀረበ (26፥9-11፤ 24፥6፤ 25፥29)?

3.* ሳኦል እንደ ፈተኛው ጊዜ ለምን አላለቀሰም (26፥17-25፤ 24፥16)?

4. ዳዊት ወደ ፍልስጥኤማውያን አገር ለምን ሄደ (27፥1)?

5. የአንኩስ አገልጋይ በመሆኑ ዳዊት ምን አገኘ (27፥4-7)? እንዴት ኖረ (27፥8-12)? የዳዊትን አካሄድ እንዴት ትመለከተዋለህ? ከ17፥37 ጋር አነጻጽር።

6. አንተ ከማያምኑት ጋር ብትተባበር ምን ችግር ሊያጋጥምህ ይችላል?

26፥6 አቢሳን፤ የዳዊት እኅት የጽሩያ ልጅ፤ 1ዜ.መ.2፥13-16።

27፥2 ወደ ጌት ንጉሥ ...ወደ አንኩስ፤ ዳዊት ከ600 ሰዎች ጋር በመጣቱ አንኩስ አሁን በደስታ ተቀበለው፤ 21፥10-15።

ሳምንት 14 ረቡዕ

1ሳሙኤል 28

1. ዳዊት ከአንኩስ ጋር በመኖሩ ምን ችግር አጋጠመው (ቁ.1-2)?

2. በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ተቃውሞ ቢኖር ከማን ጋር ትቆማለህ?

3. ሳኦል ወደ መናፍስት ጠሪ እንዲሄድ ምን ገፋፋው (3-7)?

4. ወደዚህ ዓይነት ሰው እንዳትሄድ ምን ታደርጋለህ?

5. በሳኦል ላይ ከፉ ፍርድ በምን ምክንያት መጣ (15-19)?

ቁ.2 ባርያህ የሚያደርገውን ታያለህ፤ የዳዊት መልስ አሻሚ ነበር።

ቍ.7 ዓይንጾር፤ ሳኦል ወደ መናፍስት ጠሪ ለመድረስ ከፍልስጥኤማውያን በስተጓላ ግለፍ ነበረበት (8)።

ቍ.13 እግልክት፤ ታሉ የሰግያዊውን ቤተ መንግሥት ከቡራን ሊያጠቃልል ይችላል፤ መዝ.81(82)፥6።

ቍ.14 ሳሙኤል እንደሆነ አወቀ፤ ግናቸውም ዓይነት ጥንቆላ ተከልክሉ ነበር፤ ቍ.9፤ ዘሌ.19፥31፤ 20፥27፤ ዘዳ.18፥9-12። እግዚአብሔር ሳሙኤል እንዲነሣ ቢፈቅድም፥ ሳኦል ወደ መናፍስት ጠሪ በመሄድ በኃጢአቱ ላይ ኃጢአት እንደጨመረ ግልጥ ነው፤ ቍ.15-16፤ 1ዜ.መ.10፥13-14።

ሳምንት 14 ሐሙስ — 1ሳሙኤል 29 እና 30

1. እግዚአብሔር ዳዊትን ከእስራኤል ጋር ከመዋጋት እንዴት አዳነው (29፥1-11)?
2. በእምነት ጉድለት ወይም በኃጢአት ምክንያት ከደረሰብህ ሁኔታ እግዚአብሔር አድኖህ ያውቃልን?
3. ዳዊት ወደ ጺቅላግ ሲመለስ በምን ሦስት ምክንያቶች ተጨነቀ (30፥1-6)?
4. ዳዊት ሁኔታውን ለመለወጥ እንዴት ቻለ (30፥6-20)?
5. ዳዊት ከምርኮው በማካፈሉ ስለ ትክክለኛነት ምን ትማራለህ (30፥21-31)?

30፥1 ጺቅላግ፤ 27፥6 ተመ.።

ሳምንት 14 ዓርብ — 1ሳሙኤል 31

1. የ28፥19 ትንቢት በምን አኳኋን ተፈጸመ (ቍ.1-6)?
2. ፍልስጥኤማውያን ድላቸውን ለማን ገለጡ (8-10)?
3. የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ሳኦልን ለማክበር ምን አደጋ ደፈሩ (11-13)? ለምን (ም.11)? የረዱህን ለማክበር ምን ታደርጋለህ?
4. የሳኦልን አሟሟት ከደግነቱና ከክፋቱ ጋር አስተያይ።
5. * ዮናታን፥ ሀ) ለእግዚአብሔር፥ ለ) ለዳዊት፥ ሐ) ለአባቱ ለሳኦል የነበረውን ታማኝነት ግለጥ።
6. * እግዚአብሔር በእነዚህ አሥራ ሦስት ዓመታት ውስጥ ዳዊትን ለሥርዓተ ንግሥ እንዴት አዘጋጀው?

ቍ.2 ዮናታን፤ ማንነቱን ለማስተዋል 14፥6-10፡43፤ 18፥1-4፤ 19፥1-7፤ 20፥2፡12-13፡34፡ 42፤ 23፥16-18፤ 31፥2፤ 2ሳሙ.1፥19-27 ተመ.።

ቍ.6 ሳኦል ሰይፉን መስዶ በላዩ ወደቀ፤ ይህ አሟሟት የሚያስነውር ነው። ሕይወቱን ለመመርመር 9፥2፤ 10፥1፡9፡21-24፤ 11፥6-7፡13-15፤ 15፥10-13፡20-21፡24-25፡30፤ 18፥10-12፤ 24፥16-21፤ 28፥6-7፤ 2ኛ ሳሙ.1፥23-24፤ 1ዜ.መ.10፥13-14 ተመ.።

ቍ.12 ቤትሳን፤ ከሮዶናስ በስተ ምዕራብ ከኢያቢስ ገለዓድ 30 ኪ.ሜ. የሚርቅ የፍልስጥኤማውያን ከተማ፤ መሳ.1፥27።

ሳምንት 14 ቅዳሜ — ማርቆስ 9፥1-13

መግቢያ፤ ኢየሱስ ሰው እርሱን ለመከተል ራሱን መካድና መስቀሉን መሸከም እንዳለበት ካስተማረ በኋላ «ከሰማይ ምልክት»ን (8፥11) ለሦስት ሐዋርያት አሳየ። እነርሱ በመጠኑ የክርስቶስ ግርማ ሲገለጥላቸው ነገሩን ለማስተዋል ገና አልቻሉም ነበር።

1. ሀ) የፊቱ መለወጥ፥ ለ) የሙሴና የኤልያስ፥ እንዲሁም የሦስቱ ሐዋርያት መገኘት፥ ሐ) የአብ ድምፅ፥ መ) ደመናው፥ ስለ ክርስቶስ ምን ይገልጣሉ (ቊ.2-7)?
2. ሦስቱ ሐዋርያት ገና ምን አልተረዱም (5-6፥9-11)?
3. ኢየሱስ አገልግሎቱን እንዲያስተውሉ እንዴት ረዳቸው (8-9፥12-13)?
4. «የእግዚአብሔርን መንግሥት በኃይሉ» አይተሃልን? ምን ሆነ? ምን ለውጥ በሕይወትህ አመጣ?

ቊ.1 ...ስትመጣ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ስትመጣ ክርስቶስ በክብሩ በግርማውና በንጉሥነት ይገለጣል፤ ይህም በተለይ በትንሣኤው፥ በዕርገቱና መንፈስ ቅዱስን በማፍሰሱ በገሐድ ተገለጠ፥ በተራራም ላይ በመለወጡ ደግሞ ከብሩ ታየ፤ 2ጴጥ.1፥16-18።

ቊ.4 ከኢየሱስም ጋር ይነጋገሩ ነበር፤ በሕግ መሥዋዕት ሁሉ ስለ ተመሰለና በነቢያት ስለ ተነገረ ስለ ኢየሱስ ሞት፤ ሉቃ.9፥31፤ ግቴ.5፥17።

ቊ.7 ደመና ጋረዳቸው፤ እግዚአብሔር ራሱን በምድር ሲገልጥ ብዙ ጊዜ በደመና ነበረ፤ ዘጸ.13፥21፤ 16፥10፤ 40፥35።

ቊ.13 ኤልያስ ደግሞ መጥቶአል፤ የሚል. 4፥5-6 ትንቢት በመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ተፈጽሞ ነበር፤ ግቴ.17፥11-13፤ ሐ.ሥ.7፥52-53።

ሳምንት 15 እሑድ — መዝሙር 62(63)

1. ሀ) ዳዊት በቊ.1 ምን ይናፍቃል?፥ ለ) እንደዚህ ያለ ናፍቆት መቼ ተሰምቶህ ያውቃል?
2. ዳዊት እግዚአብሔርን ለማመስገን ምን ገፋፋው (2-5፥7)?
3. ስለ ዳዊት ጸሎት፥ ሀ) ቦታ (2፥6)፥ ለ) ሰዓት (6)፥ ሐ) ውጤት (8-11) ምን ትማራለህ?
4. የምትጸልየው ብቻህን ነው ወይስ ከሌሎች ጋር ወይስ በሁለቱም ነው? ለምን?

በኤዶሚያስ ምድረ በዳ፤ ከይሁዳ በስተ ደቡብ። ካርታ ተመ.።

ቊ.4 እጆቼን አነሣለሁ (እጆቼን ወደ አንተ እዘረጋለሁ)፤ አምልኮን ወይም ልመናን የሚገልጥ የሰውነት አቋቋም።

ቊ.8 ቀኝህ (ቀኝ እጅህም)፤ ቀኝ እጅ ኃይልንና ሥልጣንን ያመለክታል።

ቊ.11 ንጉሥ፤ ዳዊት ራሱን ያመለክታል።